አንተ እና ፍልስጤም



ጸሐፊ: ዶ/ር ራጊብ አስ ሰርጃኒ

ትርጉም: ቁጥቡይን ሙሐመድ

አንተና ፍልስጤም

በዶ/ር ራጅብ አሰ ሰርጃኒ

ትርጉም፡- ቁጥቡዲን ሙሐመድ

የፍልስጤም ጉዳይ የኔ
ጉዳይ እንደሆነ
ላስተማረኝ አባቴ!

መግቢያ

አቤት የንግግር መቅለልና የተግባር መክበድ! አምላካችን አላህ እንዲህ ይላል፡- ***የዐረብ ዘላኖች “አምነናል” አሉ። “አላመናችሁም፣ ግን ሰልመናል በሉ። እምነቱም በልቦቻችሁ ውስጥ ገና (ጠልቆ) አልገባም።”*** የኢማን ንግግር ቀላል ነው። ብዙ ሰው ይለዋል። ነገር ግን ይህን ንግግሩን በተግባሩ የሚያፀና ጥቂት ነው። የኢማንን ተክል ልባቸው ላይ በተግባር፣ በትግልና በመስዋእትነት የሚተክሉ ትንሽ ናቸው።

በ**2005** እ.አ.አ መጨረሻ ላይ የዴንማርክ ጋዜጣና ሌሎች የውዱ ነብይ ﷺ ክብር የሚነካ ፅሁፍና ምስል በለቀቁና ሙስሊሞች ባሳለፉት ከባድ ጊዜ፤ ሁሉንም የነብያቸው ጥልቅ ፍቅር ነክቷቸዋል። ያ ፍቅር ነው በምስራቅም በምዕራብም የታየውን ከባድ ቁጣ የገለፀው። ከዚያህም በየቦታው ኮንፈረንሶች፣

ስብሰባዎች ተዘጋጁ። የአድማ መፈክርና ታፔላዎች በየቦታው ታዩ።

ይህንን ሁሉ ቁጣና ስሜት ከማክበር ጋር ይህን ስሜታዊ እርዳታ **(**ስሜት ላይ ብቻ የተመረኮዘ**)**፥ ተግባር ካላፀናው በስተቀር ቀላል የሆነ ጉዳይ ነው። **(**ተግባር ካልታከለበት**)** የልብን ጉዳት ጥልቀት የሚያሳይ አይደለም። ሁሌም ቢሆን የተግባር ሜዳ ከባድ ነው። ረሱልን ﷺ የመርዳት ድንበር ለርሳቸው ያለንን ፍቅር በማሳየትና ቁጣችንን በመግለፅ ብቻ የሚታጠር አይደለም። ከጅምሩ አምላካችን አላህ እሳቸውን ለመርዳት ሐላፊነቱን ወስዷል፤ በተግባርም ረድቷቸዋል። ***ባትረዱት...አላህ በእርግጥ ረድቶታል።***

ለመልዕክተኛው ﷺ እውነተኛ የሆኑ ሙስሊሞች እርዳታቸውን የሚገልፁበት፡- የእርሳቸውን መንገድ በመከተል፣ በስርአታቸው መጓዝ፣ ቀጥ ባለው ጎዳናቸው መመራት ነው።

እውነተኞቹ የነብዩ ﷺ ተከታዮች ራሳቸውን ይህንን ጥያቄ መጠየቃቸው አይቀሬ ነው፡- “ዛሬ ረሱል ﷺ በመካከላችን ቢኖሩስ ኖሮ? እንዴት ይሆን የተለያየ ሁኔታ ውስጥ ከገባው የሙስሊሙ ሁኔታና እዚህም እዚያህም ከሚፈሰው ደማቸውና ጥልቅ ቁስላቸው ጋር ምን አይነት ሁኔታ ይኖራቸው ነበር?”

የነብዩን ﷺ ህይወት (ታሪክ) በአግባቡ ለተረዳ የዚህ ጥያቄ መልስ የማይገፋ ዳገት አይደለም። ሕይወታቸው ሙስሊሞች ለህይወታቸው በሚጠቅማቸው ነገር የታጨቀ ነው። አንድም ጉዳይ አይገጥማቸውም በታሪካቸው ላይ መፍትሔውን ቢያገኙ እንጂ...

በሚቀጥሉት መስመሮች ውስጥ ለዚህች ዑማ ጥልቅ ቁስል ወደ ሆነው “የፍልስጤም ቁስል” ፊት ለፊት ለመቆም ነው። በተለይም መጨረሻ ላይ ስለታዩት ትላልቅ ጭላንጭሎች፤ እሱም የሀማስ እንቅስቃሴ ወደ ስልጣን መምጣቱ ነው (ሁሉም ፉክክሩን

በተመለከተው በ**2006** እ.አ.አ በተካሄደው ምርጫ በከፍተኛ ውጤት ማሸነፉ)። በዚህም (የዑማው ጠላቶች) ዑማው ላይ እንደአጠቃላይ በተለይ ደግሞ ፍልስጤም ላይ የተበተቡት ሴራ በግልፅ ታይቷል። የእስልምናን መንገድ በመምረጣቸው የፍልስጤም ህዝብ ላይ በጀትን በማቆምና ከበባ ውስጥ በማሰር ለመቅጣት ሞክረዋል።

በሚቀጥሉት መስመሮች ሁሉም የሚያቀውንና ሁሌም የምንሰማውን ንግግሮች ለመደጋገም አይደለም። እንዲሁም መረጃዎችን በማቅረብና ሀሳብን በመሰብሰብ ለመግለፅ አይደለም። በተጫባጩ ዐለም ትርጉም የማይገኝለትን የአስተሳሰብ ቅንጦት በየትኛውም ሁኔታ የማይቀበልውን የእስልምናን ሁኔታ ለማስረዳትም አይደለም።

አላህን ኢስላምንና ሙስሊሞችን ከፍ እንዲያደርግ እንለምነዋለን።

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ በመካከላችን ቢኖሩስ ኖሮ?

የአላህ መልክተኛ ﷺ ላይ የተሰራው አፀያፊ ምስል ምክንያት በተነሳው ቀውስ ሙስሊሞች ለታላቁ ነብያቸው ﷺ ያላቸው ፍቅር ከታየ፤ ዑማው ይህን ፍቅር ልቡ ውስጥ ተተክሎ እንዲቆይና ብርሐኑ እንዳይጠፋ መትጋት አለበት። ከክስተቱ በኋላ በነብዩ ﷺ መንገድና ብርሐን ህይወቷን መመራት አለባት።

ምንግዜም በዚህ መንገድ የመጀመርያው እርምጃ ይሄንን ጥያቄ መጠየቃችን ነው። ዛሬ በመካከላችን ቢኖሩስ ኖሮ? እስቲ ይህን ጥያቄያችን እኛ ዛሬ በምናሳልፈው ክስተትና ሁኔታ እና የአላህ መልዕከተኛ ﷺ ያሳለፉትን ክስተትና ሁኔታ በማነፃፀር መልሱን እንፈልገው። ምክንያቱም እርሳቸው ﷺ ዛሬ በአካል ከኛ ጋር ባይሆኑም መንገዳቸውን የሚያብራራ ህግጋትና ብያኔ ትተውልናል።

በዚህም ምክንያት ዛሬ ያለው ህዝበ ሙስሊም (እውነተኛ የረሱል ﷺ ወዳጅና ተከታይ የሆነው) በሚያሳልፈው የፍልስጤም ጉዳይና ስብራቷ እንዲሁም የአላህ መልዕክተኛና ﷺ ሕዝባቸው ካሳለፉት ተመሳሳይ ሁኔታ እንዴት እንዳስተናገዱት እንመለከታለን። እንደ ምሳሌም በዘጠነኛው ዓመተ ሒጅራ የተከሰተችውን እንዲሁም የረሱል ﷺ የመጨረሻ ጦርነት የሆነችውን የተቡክ ዘመቻን እንወስዳለን።

የተቡክ ዘመቻንና ከጦርነቱ በፊት ዑማው አቅሙን አምሟጦ የተሰናዳውን ዝግጅትና ማነሳሳት በአግባቡ ለተመለከተ ሰው ሙስሊሞች በዚያን ወቅት እያሳለፉት ያለውን አደገኛና ከባድ ሁኔታ ይረዳል። ጉዳዩ የሙስሊሞች ክብር (የዐለምን ስልጣኔ ከፋርስ ጋር ከተካፈለችው ሀገር) -በሮም- መነካቱ ነበር። ረሱል ﷺ በዚህ ጦርነት ሰላሳ ሺህ ጦር አሰማሩ (ነብዩ ﷺ በህይወታቸው ካዘጋጁት ሁሉ ትልቁ ጦር ነበር)። ህዝቡ በሚያሳልፈው እጅግ ከባድ

ሁኔታ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ሙዕሚኖች በነፍሶቻቸው ጂሐድ ከመውጣታቸው በፊት በንብረታቸው እንዲታገሉ አነሳሷቸው። ክስተቱ ከዚያ በፊት በየትኛውም የዑማው ጉዞ ያልታየ ትልቅ መሰጠትና መስዋእትነት የታየበት ቦታ ነበር።

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ህዝቡ በሚችለው አቅሙን አሟጦ ወደ ተቡክ እንዲወጣ አዘጋጁት። ምክንያቱም ታላቋ ሮም **(**በዚያን ወቅት**)** ሁለት መስሊሞችን በመግደሏና ወታደሮቿን በኢስላማዊ ግዛት ድንበር ላይ በመሰብሰቧ ነበር። ማለትም ገና ወደ ኢስላማዊ ሀገሮችም ሆነ ግዛት አልገባችም ነበር።

አየህን**?!** ዛሬ ረሱል ﷺ በመካከላችን ቢኖሩ ኖሮ፥ የተቡክ ጉዳይና ዛሬ ፍልስጤም የምታሳልፈው ፈተና በአንድ ዘመን ቢከሰቱ ፥ ረሱል ﷺ ወደ አንዱ እንጂ የመዝመት አቅም ባይኖራቸው ተቡክን ወይስ ፍልስጤምን የሚመርጡ ይመስልሃል**?** በዚህ ጥያቄ

አንድ አስፈላጊ የሆነ መደምደሚያ ላይ መድረስ እንፈልጋለን። እርሱም የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ያ ሁሉ አቅም የተቡክን ጉዳይ ለመፍታት ካዘጋጁ የፍልስጤም ጉዳይ ደግሞ ይበልጥ አሳሳቢና እስጊ ነው። ከተቡክ እጥፍ በሆነ ዝግጅት ለመፍትሔዋ መንቀሳቀስና ህዝቦቿን መርዳት **(**ከተቡክ ይበልጥ**)** ግዴታ ነው።

የተቡክንና የፍልስጤምን ጉዳይ ለማነፃፀር በሁለቱ ጉዳዩች መካከል የሚከተሉትን ንፅፅሮች መመልከት ይፈልጋል፦

1. የተቡክ ዘመቻ በሻም ምድር ወደ ቀይሰር እየተጓዙ ሳሉ ለተገደሉ ሁለት መልዕክተኞች ነበር **(**ሁለት ሰው ብቻ**!!)** ፍልስጤም ደግሞ የአቅሳ እንቅስቃሴ ከጀመረበት ከ**2000-2005** እ**.**አ**.**አ ብቻ ከአራት ሺህ ህዝብ በላይ ሰማእት ሆነዋል። ከነዚህም ውስጥ **20%** የሚሆኑት ከ**16** ዓመት በታች ያሉ ህፃናት

ነበሩ። (እስከ 2023 እ.አ.አ ከ30 ሺህ በላይ ፍልስጤማውያን ሰማእት ሆነዋል)።

2. ተቡክ ላይ፥ የሮም ወታደር ረሱልን ﷺ ለመጋደል እየተዘጋጀ ነበር። ገና የዐረቢያን ደሴት አልረገጠም። የሻም ምድር ላይ ነበሩ። በዚያን ግዜ ደግሞ ሻምና ተቡክ ኢስላማዊ ሐገር አልነበሩም። ፍልስጤም ላይ ግን፥ የአይሁድ ወታደር በእርግጥም እስላማዊ ሐገር ውስጥ ነው። እየወረረ ብቻም አይደለም። ይልቁንስ በፍልስጤማውያን የእስራኤል ልጆችና ቤተሰቦች እየተኩ ነው።

3. ተቡክ ላይ፥ ሙስሊሞችን ከቤታቸው አላስወጡም። ፍልስጤም ላይ ግን ከሰባ አመት በላይ በሚልዩን የሚቆጠሩ ህዝቦቿ ከቤታቸው ተፈናቅለዋል፤ እየተፈናቀሉም ነው። አላህም እንዲህ ሲል ያዘናል (መታዘዝም በኛ ላይ ግዴታ ነው)፦

ከአወጧቸሁም ስፍራ አውጧቸው። **(**በቀራ 191)

4. ተቡክ ማስፈራርያ ነበረች። ገና ጦርነት አልተካሄደም። ፍልስጤም ግን ተግባራዊ በሆነ አውዳሚ ጦርነት እየማቀቀች ነው። አምላካችን እንዲህ ሲል ያዘናል **(**መታዘዝም በኛ ላይ ግዴታ ነው**)**፡- ***እነዚያንም የሚጋደሉዋቸሁን (ከሃዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ።*** (በቀራ 190)
5. ተቡክ ላይ የተከበሩ የኢስላማዊ ቅዱስ ስፍራዎች የሉም። ይልቁንስ የበዳዮች ስፍራ ነው ያለው፤ የሰሙድ መኖርያ። ፍልስጤም ግን አቅሳ አለባት። ሶስተኛዋ ሐረም፣ የመጀመርያዋ ቂብላ፣ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ወደ ሰማይ ያረጉባት**...**

ከሁለቱ ጉዳዬች **(**በዕይታዬ**)** የአላህ መልዕክተኛ ﷺ በመካከላችን ቢኖሩና ከሁለቱ አንዱን መምረጥ ቢኖርባቸው ከተቡክ ፍልስጤምን በመረጡ ነበር።

ሁለቱም ጉዳይ አሳሳቢ **(**አደገኛ**)** ናቸው። ፍልስጤም ግን ይበልጥ እጅግ አሳሳቢና አደገኛ ጉዳይ ነው።

በዚህም መሰረት ሙሉ ዑማው በፍልስጤም ጉዳይ ያለበትን ግዴታዎች መመልከት ይኖርብናል**. . .**

ማንኛውም **(**ሁሉም**)** ሙስሊም በፍልስጤም ጉዳይ ስለሚኖረው ግዴታዎች ከማየታችን በፊት በቀጣይ ገፆች ለፍልስጤም ጉዳይ ዕይታችንን የሚያስተካክሉ አረዳዶችን እንዳስሳለን። በተለይ ሐማስ በፍልስጤም አገዛዝ ውስጥ ወደ መንግስትነት ከመጣ በኋላ የሚነሱ ብዥታዎችን **(**እንዳስሳለን**)**። ምክንያቱም መልካም አረዳድ ለመልካም ስራ ይመራል። በሌላ በኩል ደግሞ የተሳሳተ አረዳድ በመሃል መንገድ ላይ ሊያስቀምጠው ይችላል። እንዲያውም በመጀመርያው**!** በመልካም አረዳድ ያልታነፁ እንቅስቃሴዎች ውጤታቸው አመፅና አጥፊነትን ማስፋፋት ነው።

ፍልስጤምን መርዳት ምርጫ የሌለው ግዴታ ነው!

ወንድሞቻችንን ፍልስጤማውያንን መርዳት በፍላጎታችን ከምንሰራው ተጨማሪ ስራ ወይም እነርሱ ላይ ከምንሰራው ቸርነት ከፍ አድርጎት አንድ ሙስሊም ዱንያና አኺራው እንዲስተካከልለት ከፈለገ ሊተገብረው ወደ ሚገባ ግዴታ ስራ ከፍ የሚያደርገው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡-

አንደኛ፡ ሸሪዓዊ ግዴታነት፡-

ወረራ የተፈፀመባት ሙስሊም ሐገር ላይ ነፃ እስክትወጣ ድረስ መታገል ግዴታ ይሆንባታል። ማለትም ልክ እንደ ግዴታ ሰላትና ረመዷን ፆም ጂሐድም እነርሱ ላይ ግዴታ ይሆናል።

በዑለሞች መካከል ነዋሪዎቿ እርሷን ነፃ ለማውጣት የማይታገሉ ከሆነ ሁሉም አመፀኞችና ወንጀለኞች መሆናቸው ምንም ልዩነት (ኺላፍ) የለውም። የፍልስጤም ሕዝብ ሙሉ ለሙሉ ነፃ እስኪያወጧት ድረስ መታገልና መጋደል አለባቸው። የፍልስጤም ህዝብ ለዚህ ዓላማና ተልዕኮ በቂ ካልሆነ (ዛሬ እንደምንመለከተው) የጂሃድ ግዴታነቱ በጎረቤት ሐገራቶች ላይ ይዛመታል። ግብፅ፣ ጆርዳን፣ ሶርያ፣ ሊባኖስ. . . እያለ የዓለምን ሙስሊም እስኪያካልል ድረስ ይቀጥላል። የዓለም ሙስሊም ከሰባ አመት በላይ በየቀኑ የሚደርስባቸውን እየተመለከቱ ነው። ስለዚህ ፍልስጤማውያን ወንድሞቻቸውን መርዳት ግዴታ አለባቸው ማለት ነው።

አቡ ዳውድ ከጃቢር ኢብኑ ዓብዱላህና ከአቢ ጡልሓ ቢን ሰህል አል አንሳሪ እንደዘገበው የአላህ መልእክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል፡- ***“አንድ ሙስሊም ሰው መብቱ/ክብሩ በሚጣስበትና ስሙ በሚጠፋበት ሁኔታ ውስጥ እንዲወድቅ***

የሚፈቅድ አንድም ሰው የለም፤ ልዕለ ሀያሉ ጌታ አላህ የ'ሱን ረድኤት በሚሻበት/ በሚወድበት ቦታ ላይ ያዋረደው ቢሆን እንጂ። እንዲሁም አንድን ሙስሊም ስሙ በሚጠፋበት፣ ክብሩ በሚጣስበት ሁኔታ ላይ የሚረዳ የለም፤ እሱ የአላህን ረድኤት በሚፈልግበት ወቅት አላህ የረዳው ቢሆን እንጂ።

የአላህ መልዕክተኛ ﷺ የተበደሉ ሙስሊሞችን እንድንረዳ አዘውናል **(**እንዲያውም ከዚህ በላይ ማንኛውንም ተበዳይ ሙስሊም ባይሆን እንኳ እንድንረዳው ታዘናል**)**

ፍልስጤማውያን ወንድሞቻችንን ከነካው በደል በላይ ግልፅ የሆነ የለም። በአምስት አመት ብቻ **(**ከ**2000-2005** እ.አ.አ**)** ከ**40,000** በላይ መኖርያ ቤቶች ድምጥማጣቸው ጠፍቷል። ከ**100,000** በላይ ቁስለኛና ከላይ የጠቀስነው

የሰማእት ቁጥር ተመዝግቧል **(**እስከ **2023** እ.አ.አ የጋዛ **65%** የሚሆነው መኖርያ ቤት ሲወድም ከ**160,000** በላይ ቁስለኛ ሆኗል**)**።

<u>ሁለተኛ፡ ሰብአዊ ክብር፡-</u>

ሙስሊሞች ወደዚህ ጉዳይ የሚገፋቸውን በቂ ሸሪዓዊ ግዴታ ካላገኙ **(**ይሄ ተቀባይነት የለውም**!!)** ፍልስጤማውያን ላይ በሚፈፀመው ከፍተኛ ጥላቻና በደል ውስጣቸው ላይ ያለው ሠብዓዊ ክብር አይንቀሳቀስምን **(**ከነሡ ጋር የሚያዛምደን የፈለገ ነገር ቢሆን**)?**

ሠብዓዊነት አንዳንድ ከሓድያንን የተበደሉ ሙስሊሞችን ለመርዳት ሲያንቀሳቅስ በተጨባጭም በታሪክም ብዙ አይተናል፤ አንብበናልም። በአቡ ጣሊብ ስር የሚገኙ አንዳንድ ከበኒ ሐሺም የሆኑ ከሓድያን ከረሱልና ﷺ ከባልደረቦቻቸው ጋር ለሶስት አመታት በታደመባቸው ሰዓት ብዙ ርሃብና ግፍ አግኝቷቸዋል። ይህንን ረሃብና ግፍ ችለው አመታትን

እንዲዘልቁ ያደረጋቸው ነብያችን ሙሐመድ ﷺ ከጎሳቸው ስለሆነ ብቻ ነበር። በርሳቸው ﷺ መልዕክትና ነብይነት ባያምኑም የጎሳቸው ክብርና ስሜት ተንቀሳቀሰ። ይህ ክብርና ስሜት ነው ከአንድ ሙስሊም የጠንከራ እምነት ባለቤት እንጂ የማይገኝን ድንቅ ትዕግስት ያላበሳቸው።

ከዚያህ በኋላ ይሄ የበደል ስምምነትን ለማፍረስ የተንቀሳቀሱት አምስት የመካ አጋርያንና ከሓድያን ነበሩ **(**በመካከላቸው አንድም ሙስሊም የለም**)**። ከነርሱ ውስጥ ሙጥዒም ቢን ዓዲይና ሌሎችም ነበሩ። ነፍሶቻቸው እነዚህን ተበዳዮች ሳይረዱ አይቶ መቀመጥን አልቻለም ነበር።

አየህን?!. . .በዑመተል ኢስላም ላይ የሙስሊሞች ስነምግባር የከሓድያን ስነምግባርን እንዲመስልና እንዲደርስ የተመኘንበት ዘመን? ሠብዓዊነታቸው በሙስሊሞች ላይ የተንቀሳቀሰውን የነ

ሙጥሚም ቢን ዓዲይና መሰሎቹን ስነምግባር እንዲመስል (የተመኘንበትን ዘመን መምጣቱን አየህን?)

ጥንት የነበሩ ከሓዲያንና አጋሪዎች ከሙስሊሞች ይህንን ስምምነትና አድማ ለማንሳት ከተንቀሳቀሱ ፤ ዛሬ የፍልስጤም ልጆች አንገትን ተብትቦ የሚገኘውን የከበባ አድመኝነት ማን ነው ተንቀሳቅሶ ሚበጥሰው?

<u>ሶስተኛ፡ ውለታ፡-</u>

በዘመናችን ህዝቦች ሀገራቸውን ነፃ በማውጣታቸው ዓለም አቀፋዊ ውለታቸው ይነፈጋልን?

- ፈረንሳዮች ሀገራቸውን ከጀርመን ነፃ በማውጣታቸው ወንጀለኛ ናቸውን?
- አልጄሪያዎች ሀገራቸውን ከፈረንሳይ ነፃ በማውጣታቸው ወንጀለኛ ናቸውን?

- ሊብያዎች ሀገራቸውን ከጣሊያን ነፃ በማውጣታቸው ወንጀለኛ ናቸውን?

ለምንድን ነው ዓለም ላይ የሚገኙ ሐገራት ከተወረሩ በኋላ ነፃ ለማውጣት ሲታገሉ ወንጀለኛ የማይሆኑትና (እንዳውም ልጆቻቸው በጀግንነት ሲቆጠሩ ይታያል) ፍልስጤማውያን በወንጀለኝነት የሚፈረጁት? ለምንድን ነው ጀግኖቻቸውስ በአሸባሪነት የሚጠሩት? በዚህም ሩቁም ቅርቡም ሙስሊሙም ከሃዲውም የተስማማባቸው?

ይህን ሐማስና ከጀርባው ብዙሃኑ የፍልስጤም ሕዝብ የሚመራውን የትግል ጉዞ የትኛው ወግ አያፈርሰውም (ውለታቸውን አይነግገውም)።

<u>አምስተኛው፡ የፍልስጤም ልዩ ሁኔታ፡-</u>

ሸሪዓችን የትኛውንም ኢስላማዊ ሐገር ከተወረረ ሙስሊሞች ነፃ እንዲያወጧት ግዴታ

ካደረገ፤ ለፍልስጤም ምድር ደግሞ ጉዳዩን ከሌሎች እጥፍ የሚያደርገው የራሷ ልዩ ሁኔታ አላት፡-

- መስጂደል አቅሳ. . .የመጀመርያ የስግደት አቅጣጫ (ቂብላ). . .ሶስተኛው የተከበረው (ቅዱስ) ቦታ. . . የአላህ መልዕክተኛ ﷺ ወደ ሰማይ ያረጉበት ቦታ
- እርሷ አላህ ለዓለማት ብሩክ ያደረጋት ምድር
- በዳርቻዎቿ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ እውነተኞች ታጋዮች ይገኛሉ። ኢማም አህመድ ከአቢ ኡማማ እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል ***“ከሀዝቦቼ መካከል አንዲት ቡድን በጠላቶቻቸው ላይ ድል በመንሳት የበላይ ሆነው ሐይማኖቱን ከማስቀጠል አይወገዱም፤ የሚቃወሟቸውም ካጋጠማቸው መከራ በስተቀር ምንም አይጎዷቸውም። በዚህ ሁኔታ ላይ ሳሉ የአላህ ትእዛዝ እስኪመጣቸው ድረስ። የአላህ***

መልእክተኛ ሆይ የት ናቸው? "በበይት አል-መቅዲስ እና በበይት አል-መቅዲስ ዳርቻ" አሉ።

- እርሷ የመሰብሰቢያና የመቀስቀሻ ቦታ ናት። ኢብኑ ማጀህ ከመይሙና እንደዘገበው፡- **“**የአላህ መልዕክተኛ ሆይ**!** ስለ በይተል መቅዲስ ንገሩን**”** አልኳቸው**. . .** እሳቸውም ﷺ ***“የመሰብሰቢያና የመቀስቀሻ ምድር”*** አሉ።

ምንአልባት አላህ በዚህች ምድር ላይ ይህ ሁሉ ትላልቅ መገለጫዎችን ያደረገባት ቀዳሚውን **(**የሚመጣውን**)** በሚያውቅበት ዕውቀቱ እስከ ትንሳኤ ድረስ የትግል ማዕከል ስለሆነች ይሆናል። ከዚያ በፊት ፋርሶች **(**ፐርዢያዎች**)** ተመጀች፣ ከዚያ ሮማውያን**. . .**ከዚያ ጊዜያቶች አልፈው መስቀለኞች ወረሯት፣ ከዚያህም ምዕተ ዓመት ተቆጥሮ እንግሊዞችና አይሁዶች ተመጀች። **. . .**እስከ ትንሳኤ

ቀን ድረስ የትግል ማዕከል ትሆናለች። አላህ ለሙስሊሞች ካለው እዝነት **(**ሙስሊሞች**)** ወደርሷ ነፍሶቻቸው እንድትጓጓ ይህን ሁሉ መገለጫ አደረገባት። ፍልስጤም አትወረርም የሙስሊሞች ነፍስ ወደርሷ የተንቀሳቀሰች ቢሆን እንጂ**. . .!**

ስለዚህ ፍልስጤም የዑማው ኢማን መመዘኛ ናት። ዑማው በፍልስጤም ጉዳይ ላይ በከፍተኛ ጉጉት ከተንቀሳቀሰ ይህ የኢማን ጥንካሬ ምልክት ነው። ዑማው በፍልስጤም ጉዳይ ከተዘናጋና ወደኋላ ከቀረ የኢማን መድከም ምልክት ነው። ድል ደግሞ ከደካማ ኢማን ጋር አይመጣም።

<u>አምስተኛ፡ ለብሔራዊ (የጋራ) ደህንነት፡-</u>

ፍልስጤም ላይ የሚካሄደው የፅዮናውያን ዕቅድ ከፊት ለፊት ሆኖ የሚጋፈጠው ሀይል መኖሩ ለጋራ ደህንነት ግዴታ ነው። ለፍልስጤም ብቻ

አይደለም። ለጎረቤት ሀገራትም ብቻ አይደለም። ዓለም ላይ ለሚገኙ የሙስሊምና ዓረብ ሀገራት በሙሉ አስፈላጊ ነው። ግብፅ ደግሞ ግንባር ቀደሟ ነች።

የሐማስ እንቅስቃሴ አሁን ላይ ፅዮናውያን ላይ የዘመተ የጦሮች ሁሉ ቁጥጮ ሆኗል። ይህ ሐይል **(**የሐማስ እንቅስቃሴ**)** ካልተጠናከረ፥ እንዲሁም ከተሸነፈና በፍልስጤም ላይ ኢስላማዊ ዕቅድ ከደከመ፤ ከዚያህም እኚህ ታጋዮች ከወደቁ አይሁድ ከፍልስጤም ውጪ ወዳሉ የሙስሊም ሀገራት ፊቱን ያዞራል።

አይሁዶች የመለጠጥ መርሓቸው ላይ የገነቡት የቀኝ ግዛት ዕቅዳቸው ፍልስጤም ላይ ብቻ እንደማይበቃቁ ሚስጥር አይደለም። አይሁድም ይህን ለመደበቅ አይሞክርም። አለበዚያማ ከናይል ወንዝ እስከ ኤፍራተስ የተዘረጋውን የታላቋን እስራኤል ካርታ በየምኩራቦቻቸው ባልሰቀሉትና

ይህንን ግምታቸውንና ፍላጎታቸውን የሚደግፍላቸውን ሐሳብ በየሐይማኖታዊ ድርሳናቶቻቸው ላይ ባላሰፈሩት ነበር። የሰይናእ ወራረ ከኛ የራቀ አይደለም። ሊባኖስ ላይ ያደረጉትም ዘመቻ እንዲሁ። ይህ የወራሪው እንቅስቃሴ ሙስሊሞች ሁሌም በአይናቸው የሚመለከቱት ተጨባጭ ሆኗል። ለዚህ የአይሁድ ወራሪ ሐይል ያለ ተቃዋሚና ታጋይ እንዲፋፋ ከተፈቀደለትና ከተተወ ከናይል እስከ ኤፍራተስ ወዳለው ሐገራቸው ማሰባቸው አይቀርም። እሷን እውን ካደረጉ ከርሷ ውጪ ወዳሉት ያስባሉ። የአይሁድ የመለጠጥ ህልም የሚያበቃ አይደለም።

ሌላው አይሁድ ዐለም ላይ ያሉ ኢስላማዊ ሀገራትን ለመቆጣጠርና ለመክበብ ያለውን ፍላጎት ከሚያረጋግጡ ነገራቶች ውስጥ ባሳለፍነው የምዕተ ዓመት መንፈቅ ላይ ራሳቸውን እንደ ሐገር ሲያውጁ ያቀዱት ዕቅድ ነው። በ**1948** እ.አ.አ መጨረሻ አከባቢ ቤን ጆርዮን **(Ben Gurion)** ይፋ

ባደረገው **“ጫፉን ማጠናከር/መጎተት”** የተሰኘው ዕቅድ ነው። ይህ ዕቅድ ዋና ዓላማው ዓረብና ሙስሊም ሀገራትን በዚሁ መልኩ መክበብ ነበር፡-

- ኢስላማዊና ዐረብ ሐገራትን ከበው የሚገኙ ዐረብ ያልሆኑ ጥንታዊ ማንነት ካላቸው ጋር ስምምነት መፍጠር፤ በዚያን ጊዜ የአይሁድን አይን ከሳቡ ሀገራት ውስጥ፡- ቱርክ፣ ኢራን **(**ከኢስላማዊ ንቅናቄ ከመጀመሩ በፊት**)**ና ኢትዮጵያ ናቸው።
- ዐረቡ ዓለም ውስጥ የሚገኙ አናሳ ቁጥር ያላቸው ህዝቦች የማንነትና የዘር ጉዳይን ማስነሳት ነው። ይህም የሚሆነው በነዚያ አናሳ ቁጥር ባላቸው ህዝቦች ውስጥ በመሪዎቻቸው **(**በሀገር ሽማግሌ/ የጎሳ መሪ**)** በኩል ነው። **(**ኩርዶች በኢራቅ፣ የደቡብ ሱዳን ነዋሪዎች፣ ድሮዝና ኩርድ በሶርያ**)**

ይህን ዕቅዳቸውን ከተገበሩ በኋላ በ**1960** እ.አ.አ በዚያን ወቅት የኢስራኤል የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበረችው ጎልዳ ሜር **(Golda meir)** “ዐረቡ ዓለምን ከበው የሚገኙ ለአረቡ ዓለም አጥር እንዱሆኑ “ክቡ ስምምነት” እንዲተገብሩ ለማድረግ የማሳመኑን ሂደት በድል ተወጥተናል” ስትል በኩራት ይፋ አድርጋዋለች።

ይህ ስትራቴጂያቸው እስካሁን ድረስ የኢስራኤላዊን ጭንቅላት ተቆጣጥሮት ይገኛል። ሙስሊም ሀገራትን ከበው የሚገኙ ሀገራቶች ጋር የሚያደርጉትን ስምምነት እየተመለከትን ነው። ፍልስጤም ብቻ ሳይሆን ሙሉ ዑማውን ለመቆጣጠር። በዚሁ እሳቤና አቅጣጫ ከህንድና ሞሪታንያ ከመሰሉ ሀገራት ጋር የምታደርገውን ግንኙነት እንዴት እንደምታስተካክል አስተውል። የዚህ ጉዳይ አሳሳቢነት ይበልጥ ግልፅ የሚሆንልህ በዘጠናዎቹ መጀመርያ ላይ ከሶቪየት ህብረት ነፃ የወጡ ኢስላማዊ ሪፐብሊኮች ጋር የመጀመርያና ግንባር

ቀደሟ ሙሉ የሆነ ዲፕሎማሲ የጀመረች ሀገር ኢስራኤል መሆኗን ስታውቅ ነው።

አይሁዶች ውስጣዊ ሆነ ውጫዊ የፖለቲካ አካሄድና መንገድ ከእስልምና ካላፈነገጠ በስተቀር ከሙስሊም ሐገራት ጋር መስማማትም ሆነ ሙስሊም ሀገራት ላይ የሚገኙ ጎሳዎች **(**ዘር**)** ጋር የብጥብጥን አጀንዳ ማስፋፋት እንደማይችሉ ከኛ የሚጠፋ ጉዳይ አይደለም።

ስለዚህ እኛ ወንድሞቻችን ፍልስጤማውያንን ስንረዳ ወይም እገዛ ስናደርግላቸው በነርሱ ላይ ውለታ እየዋልን አይደለም። ነገር ግን በመጀመርያ ደረጃ ራሳችንን እየረዳን **(**እያዳንን**)**፤ ሳናስበው አንገታችን ላይ እየተጠመጠመው ያለውን የከበባ ፖለቲካ ለመዳን እየተሯሯጥን ነው። ይህ የፖለቲካ አካሄድ ነው በሚያሳዝን ሁኔታ ኢራቅን እስኪያንበረክካት ድረስ፣ ሊብያ የምዕራባውያንን ቅድመ ሁኔታዎች እስክትቀበል ድረስ ትተነው ከግብ እንዲደርስ

ያደረግነው። አሁንም ፍልስጤም ላይ ታጋዮችን ችላ በማለት፣ ባንዲራውን ከፍ የሚያደርጉትን በመተውና ፅዮናውያኑን ጣኦት በመጀመርያ ደረጃ የሚታገለውንና የሚገድበውን ሀይል በማፍረስ ህዝቡን በማንበርከክ ከግባቸው እንዲደርሱ እየተደረገ ይገኛል።

ከላይ እንዳየነው. . .ዱንያ ላይ ብቻ አይደለም ነፃ ምንወጣው። ይልቁንስ ከአኺራ ቅጣት ለመዳን የተወረረችውን ኢስላማዊ ሀገር ነፃ ማውጣትና ወንድሞቻችን መርዳት በኛ ላይ አማራጭ የሌለው ግዴታች ነው። በሌላ በኩልም እንዳየነው ተበዳይን እያየን የእርዳታ እጃችን ሳንዘረጋለት የሠብአዊ ክብር የመጥፋቱ ምልክት ነው።

ሐማስን ለምንድን ነው ሚፈሩት?

እዚህ ጋር ቆም ብለን አህጉራትና ሀገራት ሐማስ (ሁሉም ፍትሐዊነቱን በተመለከተው ምርጫ ማሸነፉን ተከትሎ) ወደ ስልጣን እንዳይመጣ የተረባረቡበትን ሚስጥር ማስተንተን ግድ ይለናል። አንድ ማንኛውም ባለ አዕምሮ፡- ለምንድን ነው የምዕራባውያኑ ማህበረሰብ (በክንፎቹ አሜሪካና አውሮፓ) ከመሰረታዊ የእድገት ተግዳሮቶች ያልተላቀቀውን የሐማስ ሙከራን የሚሞክረው? እንዲሁም ከበስተፊታቸው ወራሪው በሚታወቀው አሻራው (ለማክሰም) የሚታገለው? በሌላ በኩል ፍልስጤምን ካየናት (ሳትወረር በፊትም) ከ26 ሺህ ኪሜ ስክዌር የማታልፍ ትንሽዬ ሀገር ናት። በችግርና በተግዳሮቶች የተተበተበው ስልጣን ላይ ኢስላማዊ መንግስት (ሐማስ የሚወክለው) ቢወጣ በየትኛው የምዕራባውያን ጥቅም ላይ ነው አሉታዊ ተፅዕኖ ሚያሳድረው?

ለዚህ ጥያቄ መልስ ኢስላማዊ መንግስትን የሚወክለውን (የሀማስ) ወታደራዊ ሐይል ማድረግ አይቻልም። ይህ ወታደራዊ ሐይል የፈለገ ቢጠነክር (ያለፈው የስልጣን ባለቤት) ፈትሕን ሊበልጥ አይችልም። (ኢስራኤል ከታጠቀችው ኒውክለር መሳሪያዎችና ሌሎቹን ማነፃፀር ትተን ማለት ነው።)

ዐለም አለኝ በምትለው ሰበቦች ሁሉ የቻለችው ብታደርግም፤ በዚህኛው ዙር በፍልስጤም ሜዳ ላይ ለሚታየው ፖለቲካዊ፣ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ሆነ ሌሎች ችግሮች መፍትሔያቸው ኢስላማዊ በሆነ መንገድ ነው ብሎ የሚያምነውና የኢስላም መገለጫዎችን (ምልክቶችን) ከፍ የሚያደርገው ሀማስ ወደ ስልጣን መጥቷል። ይህ በራሱ በዘመናችን የሀገራት የፖለቲካ አመራሮችና ሊቃውንቶች ዘንድ በነዚህ ምክንያት ተቅባይነት የለውም፡-

1. **ጉዳዩ ሰልሟል...ውጤቱ፡-**

የሀማስ ማሸነፍ በአጭሩ "የፍልስጤም ጉዳይ ሰልሟል" ማለት ነው። ይህ ደግሞ በሐገራት የፖለቲካ ትርጓሜ ባህል እጅግ በጣም የከፋ አደገኛ ነገር ነው። ምክንያቱም የጨዋታው ሚዛን ለፅዮናዊ ኃይል ምቾትና መፋፋት አጋዥ የነበረው አድካሚ ዕቅድና ለድርጊቱ መድረክ ፈጣን ዝግጅት የነበረውን በረጅሙ ታሪክ ድምጥማጡን ስለሚያጠፋው ነው።

ሀ. ጉዳዩ ሰልሟል...የመጀመርያው መፍትሔ

የፍልስጤም ጉዳይ መስለም ይህን ችግር ስር ነቀል በሆነ መንገድ እንዲፈታና አደራውን ለባለቤቶቹ እንዲመለስ እንዲሁም ከሰባ አመታት በላይ የተቆጣጠረውን ወራሪ ኃይልን ለማጥፋት የመጀመርያው ትክክለኛ መንገድ ነው።

የፍልስጤምን ታሪክ ያስተነተነ (ፍልስጤም) ወደ ሙስሊሞች ስትመለስ የኖረችው ታማኝ በሆኑ ምዕመናን እጅ መሆኑን ያለ ድካም ይረዳል ። በእውነተኝነት የእስልምናን ባንዲራ ከፍ የሚያደርጉና

የአምላካዊ የድልን መስፈርት በሚያሟሉ እጆች ነው። ጠላቶቻችን ታሪካችንን ያነባሉ። እንዴት ድል እንደምናደርግ (በሚያሳዝን መልኩ ከኛ በላይ) ያውቃሉ። በእርግጠኝነት ዑመር ኢብኑል ኸጣብ ለወታደሮቹ የተናገረውን "ሙስሊሞች ድል የሚያደርጉት ጠላቶቻቸው አላህን በማመፃቸው ነው። እንዲህ ባይሆን ኖሮ እነርሱ ላይ ኃይል ባልነበረን ነበር። ምክንያቱም ቁጥራችን እንደ ቁጥራቸው፤ ዝግጅታችንም እንደ ዝግጅታቸው አይደለም። በወንጀል ከተስተካከልን (እኩል ከሆንን) እኛ ላይ በኃይልና ዝግጅት ብልጫ አላቸው። በብልጫችን (በኢማን) ካላሸፍናቸው በኃይል ብቻ ልናሸንፋቸው አንችልም።" የሚለውን ንግግር በደንብ ያውቃሉ።

እንደሚታወቀው ይቺ ኡማ ከጌታዋ ጋር ወደነበራት መልካም ግንኙነት ካልተመለሰች፣ በልጆቿ መካከል የወንድማማችነት ገመድ ካልዘረጋችና በምትችለው

አቅም አቅማቸውን ለማጠንከር ካልታገሉ ...ድል ልታደርግ አትችልም።

በመቀጠል አይሁድና ከጀርባዎቻቸው ያሉት ሀይሎች ሀማስ የታጠቀው ኃይል ብዙም አያሳስባቸውም። የሚያስጨንቃቸውና በጉጉት የሚከታተሉት ኢኽላሳውን (ለአላህ ያላቸው ፍፁማዊነት)፣ እውነተኝነታቸው፣ ቆራጥነታቸው፣ በአላህ መንገድ ላይ ለመሞት ያላቸውን ውዴታ፣ የጀነት ፍላጎታቸውን፣ የጀሃነም ሽሽታቸውን፣ በትንሹም በትልቁም ለአላህ ህግ ያላቸው ጥብቅነት...ነው። ጠላት ይህን በተመለከተ ጊዜ ሙሉ በሆነ እርግጠኝነት ለነዚህ የአላህ ባሮች ቦታው ከተተወ አይደለም ፍልስጤምን ሙሉ ዓለምን እንደሚያስተዳድሩ በእርግጠኝነት ያውቃሉ። ይህ በሙስሊሙ ታሪክ በተደጋጋሚ ታይቷል፤ ተከስቷልም።

ዛሬ ጠላቶች በሀማስ ስልጣን መያዝ እንደተበሳጩት ትላንት ልክ በተመሳሳይ በ1992 እ.አ.አ አልጄርያ ላይ

“ኢስላማዊዎች” 90% በማምጣት ባሸነፉ ጊዜ ተበሳጭተዋል። የዚያን ጊዜ ዱንያ በአንድ እግሯ ቆመች። ኢስላማዊው መንግስትን (በነፃነት ሐገሯ በፈረንሳይ መሪነት) እስኪያወርዱ ድረስ አልተቀመጠችም ነበር (አልጄርያም እንዲሁ ሌሎች ሀገራቶች ላይ ተፅዕኖ ማሳደር የምትችል ኃያል ሀገር አልነበረችም፤ አይደለችምም)። የአልጄርያ ሕዝብ እስካሁን ዴሞክራሲን በመምረጡ ከባድ ዋጋን እየከፈለ ይገኛል።

ለ. የታጋዮች ግንባር መስፋትና መለጠጥ፦

ከጉዳዩ መስለም ውጤቶች ውስጥ ሌላኛው ጠላት በኛና በነሱ መካከል በሚደረገው ጦርነት እንዲነካኩና እንዲገቡ የማይፈልጋቸው ብዙ ክፍሎችና ሀይሎች እንዲገቡ ያደርጋል።

በደንብ ለማብራራት በዐለም ላይ የሙስሊሙ ቁጥር 1300 ሚልየን (1.3 ቢልየን) ነው። ከዚህ ውስጥ ዐረብ 300 ሚልየን ብቻ ነው። የዚህ ግንባር

መስፋፋትና መለጠጥ ተጨባጭያዊ ግዴታ ነው (አይቀሬ ነው)። ምክንያቱም የፍልስጤም ጉዳይ ከላይ ባሳለፍናቸው ገፆች እንደተመለከትነው በሙስሊሙ የእምነት ጉዳይ ውስጥ የሚገባ ነው። የትኛውም ቋንቋና የደም ትስስር ቢያገኛቸው እንኳ! ጠላት (ወደ ፍልስጤም ጉዳይ እየተመለከተ) እንደ ፓኪስታን፣ ቱርክ፣ ኢራን፣ ኤንዶኔሻያን...የመሳሰሉና ሌሎች በወታደራዊ አቅምና በሰው ሀብት የታጨቁ ሀገራትን ተደርድረው ሲመለከት የሚኖረውን ሃሳብ ምን እንደሚመስል አስብ! በዚህ ጊዜ ይህ ጠላት ራሱን የተለያየ ዝግጅት፣ ከፍተኛ አቅም እንዲሁም ሰፊ የሆነ የመሬት ይዞታ ካላቸው ጋር እንደሚጋጠም ያስባል።

ጠላቶቻችን ከጥቂት ጊዜያት በፊት የሙስሊሞችን (ዐረብ የሆኑትም ያልሆኑትም) ስሜት መንካት ምን እንደሚያመጣ በዴንማርክ የጋዜጣ ገፆችና ሌሎች ላይ ውዱን መልዕክተኛ ﷺ ባነወሩ ጊዜ ተመልክተውታል። ለፍልስጤም የሙስሊሞች እርዳታና ቁጣቸው ከዚህ ያነሰ እንደማይሆን በደንብ

ያውቁታል። በተለይ የጉዳዩ አረዳድ ትክክለኛና ሸሪዓዊ ዕይታው የተስተካከለ ከሆነ!

ሐ. አላህን የሚሹ ወታደሮች፦

ሌላው የፍልስጤም ጉዳይና ሌላው የዑማው ዕጣ ፈንታዎች (በጠላት ዕይታ) አደገኛ ውጤት መካከል፥ ይህንን ጉዳይ ተሸክመው የሚሄዱትን የወታደሮች ዓይን ወደ ርካሽ ዱንያዊ ሸቀጦችና ምርኮዎች ሳይሆን የአላህ ውድ ዕቃ ወደ ሆነችው ወደ ጀነት ታደርጋለች። ይህ አላህን ግቡና አኺራን መርጊያው (መዳረሻው) ያደረገ በመጀመርያው የሚታነፅበት ነው። ይህንንም (ጀነትን) ሙዕሚን መሆኑን ሲያውጅ የሚሰጠው ማረጋገጫና ማጠንከርያ ነው። ***አላህ ከምእመናን ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ገነት ለእነሱ ብቻ ያለቸው በመኾን ገዛቸው። በአላህ መንገድ ይጋደላሉ። ይገድላሉምም፤ ይገደላሉም። በተውራት በኢንጂልና በቁርአንም (የተነገረውን) ተስፋ በእርሱ ላይ አረጋገጠ። ከአላህም የበለጠ በኪዳኑ የሚሞላ ማነው በዚያም በእርሱ***

በተሻሻጣችሁበት ሸያጫችሁ ተደሰቱ። ይህም እርሱ ታላቅ ዕድል ነው። (ተውባ 111)

የፍልስጤም ጉዳይ የእስላማዊ እምነትን በአግባቡ ከያዘና ከተላበሰ ወታደሮቿ ስምምነታቸው ከአላህ ጋር የተፈፀመ ይሆናል ማለት ነው። ከመካከላቸው አንደኛውም ቢሆን ለእፍኝ ዶላር ሲል የአላህን ሐቅ በፍልስጤም መሬት ላይ ለመሸጥና ለመተው ከንቱ የሆነ ዱንያዊ ስምምነት አያደርግም።

የዚህ አይነት ማንነት ያላቸው ወታደሮች ለጠላት (በተለይ ለአይሁድ) አዳጋችና ከባድ ነው። ምክንያቱም ሀሊናቸውን መግዛት እንዲሁም ፊታቸውን ከአኺራ ዘወር ማድረግ አይቻልም። ጀነትን የተመለከተና ጠረንዋን ያሸተተ እንዴት ሆኖ ከአሜሪካ ወይም ከኢንግሊዝ ...ምንዳን ይፈልጋል?

የፍልስጤም ጉዳይ ለዚህ መቅዘፍት የተዳረገው በጉዳዩ ልጆች (ሕይወታቸውን በትግልና በምሽጎች ውስጥ የጀመሩ) ዘንድ ገንዘብና የዱንያ

ጥቅማጥቅም ባሸነፈ ጊዜ ነው። የዚያን ግዜ ነፍሶች ተቀየሩ፣ መዳረሻቸውና አቅጣጫቸው ተቀየረ። አንዳንድ ያለፉት ታጋዮችን የፍልስጤም ጉዳይን ለመሸጥና ለማክሰም እንደ መንገድና እንደ መሳርያ ተጠቀሟቸው።

ረሱል ﷺ ህዝባቸውን ከዱንያ ፈተና ባስጠነቀቁ ጊዜ ዕውነት ተናገሩ። ቲርሚዚ ትክክለኛ በሆነ ዘገባ ከዐምር ኢብኑል ዐውፍ ረዐ እንደዘገቡት ረሱል ﷺ እንዲህ ብለዋል **“በአላህ ይሁንብኝ! እኔ እናንተ ላይ ድህነትን አልፈራም። ነገር ግን የምፈራው ዱንያ ከበስተፊታችሁ ለነበሩት እንደተከፈተችው ለእናንተም ተከፍታ፤ እነርሱ ለርሷ እንደተሸቀዳደሙ እናንተም ለርሷ ተሸቀዳድማችሁ፤ እነርሱን እንዳጠፋቻቸው እናንተን እንዳታጠፋችሁ ነው (ምፈራው)”**

2. ከተደጋጋሚ ሙከራ ያለ ፍራቻ

ሐማስ ወደ ስልጣን በመምጣት ሂደት ሙከራው ከተሳካ (ምንም እንኳ ግልፅና እረፍት አልባ ከሆነው የወራሪው አዳጋችነትና ካለው የአቅም ውስንነትና ድክመት ጋር በሌሎች ኢስላማዊ ሀገራት ላይም ይህ ድል ለተደጋጋሚ ሙከራ ሀይልና ድፍረት ይሆናቸዋል። አሁን ላይ በሙስሊሙ ዓለም ላይ ያለውን የእስላማዊ ንቅናቄ ስፋቱን እናውቀዋለን። እኚህ ንቅናቄዎች ሐማስ ባሳለፋቸውና በሚያሳልፋቸው አይነት አዳጋች ጉዞዎች የተቆራኘ ከሆነ እስላማዊ መንግስት የመሆናቸው ዕድል የሰፋ ነው።

በተለያዩ ሙስሊም ሐገራት ላይ እስላማዊ እንቅስቃሴን የሚያንፀባርቁ ሐይሎች ወደ ስልጣን መምጣታቸው ለምዕራባውያን፥ ሙስሊም ሀገራት ላይ ላላቸው ጥቅም ምን ያህል አስፈሪና አስጊ ሁኔታ ውስጥ እንደሚከታቸው ሚድበቅ ጉዳይ አይደለም።

3. <u>የአመፀኞች መዝገብ መጋለጡ</u>

ከላይ ካሳለፍናቸው በተጨማሪ የሀማስ በኢስላማዊ ማንነቱ ስልጣን መያዙ ያለፈውን መንግስት ስምን ያጠለሹ ጥቁር መዝገቦች ይገለጣሉ። ምክንያቱም የሀማስ እጅ ንፅህናና ከህዝብ ገንዘብ ያለው ቁጥብነት ያለፈው መንግስት ያሳለፈውን አስነዋሪ ድርጊቶች ያጋልጣል።

እውነቱን ለመናገር ያለፈው መንግስት ውስጥ የነበረው የአጭበርባሪነት መዝገብ ከተደበቁ ሚስጥሮች አልነበረም። ቅርቡም ሩቁም የተመለከተው፤ የፍልስጤም ዳኞች የሚቀባበሉት ጉዳይ ነው። ይህ መዝገብ በ1996 እአአ መንበረ ስልጣኑን ከተቆናጠጠ ጀምሮ (አላህ ያዘነለት ሲቀር) የጀመረና የቆየ የጥንት ነው። ለዚህም ማሳያ በ1997 እአአ (ስልጣን ከያዘ ከአንድ አመት በኋላ) 326 ሚልየን ዶላር እንደተሰወረ ይፋ ተደርጎ ነበር። በዚህ

ልክ ያለ ገንዘብ ተሰወረ ሲባል ምንም ለማለት እንደሆነ እንጃ!

ይህ ዜና -ሌሎችም እጅግ ብዙ ብዙ የሚያስደነግጡ- ውዱ ነብያችን ﷺ ዑመታቸው ላይ ይፈሩት የነበረውን የገንዘብን ፈተና አስጊነት ያረጋግጥልናል። ኢማም አህመድ ከካዕብ ኢብኑ ዒያድ ረዐ እንደዘገበው የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ሲሉ ሰምቻለው ብሏል **“ለሁሉም ህዝቦች ፈተና አለባቸው። የህዝቦቼ ፈተና ገንዘብ ነው።”**

የምድርና የሰማይ በረከት (ሲሳይ) (አላህ ለከተማዋ ባለቤቶች በርሱ ካመኑና እርሱን ከፈሩ ቃል የገባላቸው) በፍልስጤም ኢኮኖሚ ላይ ከወረደ፤ አላህን በምትፈራና ከሐራም በምትቆጠብ እጅ ላይ ምትዟዟር ከሆነ...ይኼ የሚሆን ከሆነ ያለፈው መንግስት ላይ ያለ አጭበርባሪነትና አስከፊው ገፅታ ብቻ አይደለም ሚጋለጠው፤ ይልቁንስ ከበዋት የሚገኙ ሙስሊም ሐገራት ላይ የሚኖሩ ህዝቦች

ኢኮኖሚዋን ያደቀቀውንና ያቀጨጨውን መመልከት ይጀምራል። ሁሉም ሙስሊሙ ዓለም (ብዙሃኑ ከሚስለው በተቃራኒ) ተፈጥሮ በሰጣት ነገር ባለፀጋ እንደሆነች፣ በረከቱ ዶፍ እንደሆነ፣ መሬቶቿ አላህ ቃል የገባላትን ነገር ለማውጣት አስማተኛ ዱላ እንደማትፈልግ (ሁሉም) የዛኔ ይረዳል። ይልቁንስ ውዱእ ያደረገች፣ የሰማይ ምሬትን የጨበጠች እጅ ነው ምትፈልገው።

ለዚህ ነው አመፀኞች የአሳማሪዎችን (ሙስሊሆች) ከፍ ማለትና ማበብ መሸከም የማይችሉትና የማይፈልጉት። ምክንያቱም በዚህ ከፍታና ማበብ መሬት ስር ተቀብሮና ተሸፍኖ እንዲቀር የሚፈለገውን አመፀኝነትን ያጋልጣል።

<u>አንድን ስህተት (ውድቀትን) ራሱን መደጋገም የአዕምሮ አለመኖር ምልክት ነው!!</u>

አንድ ታዋቂ የሆነ አባባል አለ። ያ አባባል መግለፅ የሚፈልገው ውድቀት (ስህተት) በታሪክ ወደ ጥፋት የሚወስድ የመጀመርያ ሙከራ ነው። ሁለተኛ ሙከራ ላይ የሚደረግ ስህተት (የመጀመርያውን ራሱን ስህተት የሚደግመው ከሆነ) ጫወታ (ቀልድ) ነው። ማለትም አንድ ህዝብ አንድን ጉዳይ ለማሳካት ተስማምተው ይህ ጥረታቸው ካልተሳካ፤ ይህ ስህተታቸው ምቹን አጋጣሚ ወደ ማሳጣት ወደ አደጋ ይወስዳቸዋል።

ነገር ግን ከነሱ በኋላ ሌሎች መጥተው ወደየትም የማያደርሰውን ያንኑ መንገድ የሚጓዙ ከሆነና እነሱ ሞክረው የወደቁበትን ተመሳሳይ ሙከራ የሚያደርጉ ከሆነ ይህ ድግግሞሽ ጨዋታ ተደርጎ ይቆጠራል። ከቀደሟቸው ሰዎች ስህተትና ውድቀት ምንም ነገር

ባለመማራቸው በነዚህ አዕምሮዎች ላይ መቀለድና ማሾፍ ይገባቸዋል።

ይህን ምሳሌ እኛ ለፈልግነው ጉዳይ ላይ ስናስቀምጠው፡- እንዴት ሆኖ ያለፈው የፍልስጤም መንግስት ያለፈበትን የድርድርና የስምምነት ሂደት እንዴት አሁንም ሐማስ እንዲተገብረው ይጠየቃል? የፍልስጤም ጉዳይ ከኦስሎ ጀምሮ ከርሷ በኋላም ከሰላሳ አመት በላይ የተሄደበትንና ህዝቡ በርሷ መሄድ የሰለቸውን የድርድርና የስምምነት ሂደት (ለፍልስጤም ጉዳይ) ምን አስገኘ?

ፍልስጤም ጉዳይ መዝገብ ላይ የተቆለለው ስህተትና ውድቀት ማንኛውም ጤነኛ አዕምሮ (ዋሀይ ላይ ያልተሞረከዘ ዕይታ ቢኖረው እንኳ) በሰላምና በድርድር የሚደረግን ሂደት ይከለክላል።

ከዚያህም አንድ ባለ አዕምሮ፣ እስራኤል (እንዲሁ በፍቃዷ) አንድ ሀገር ሙሉ ለሙሉ የማስተዳደር ሲባል ምትተገብራቸውን ማለትም ከመሬቱ

የሚከላከል የታጠቀ ወታደር፣ ወደፈለጉበት የሚፈልጉ የሚወጡበትና የሚገቡበት ይህንንም የሚቆጣጠሩ... ነፃ እውነተኛ ፍልስጤማዊ ሀገር እንዲመሰረት ትፈቅዳለችን?

አሜሪካ (ለእስራኤል ጥቅም ስትል) ርቀት ቢኖራቸውም እንኳ ግባቸው እስራኤልን ስለሚያሰጋ እስላማዊ ሐገሮችን እንደ ኢራን፣ ኢራቅ፣ ፓኪስታን... ያሉ በዘመናዊ መሳርያ እንዳይታጠቁ ከከለከለች፥ ታዲያ እራሷ እስራኤል የሃይል ባለቤት የሆነችን የታጠቀችን ሀገር እንዲመሰረት ትፈቅዳለችን? አይሁድ እንደ ስደተኛ መጠለያ የተለያየና የተከፋፈለ ሀገር ካልሆነ በስተቀር እንዲመሰረት ልትፈቅድ አትችልም።

እዚህ ጋር ማስታወስ ያለብን ሃማስ የመጨረሻውን ምርጫ ታጋይነትን በሚያቅፍ መለሳለስን በሚጠየፍ ፕሮግራሚ ነው የገባችው። ያሸነፈችውም ህዝቡ ከ20 ዓመታት በላይ ፈትህ ያቀፈችውን ሰላማዊ መንገድ

በመቃወምና የሃማስ ፕሮግራምን በማመኑንና በመደገፉ ነው። (ፈትሕ) ወዴት መሆኑን ባናውቅም ያለፈውን መንገዷን መቀጠል ትፈልግ ነበር። ፍልስጤማውያን የፈትሕን ፕሮግራም ሞከሩ። ከዚያህም ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ሐማስን መረጡ። ስለዚህ በምርጫ ያሸነፈው ፓርቲ ሕዝቡ በፕሮግራሙ ሰበብ የመረጠውን እንዲቀደው ይፈልጋልን? በምርጫው (በፕሮግራሙ ሰበብ የተሸነፈውን ፈትሕ) የከሰረውን የሱን ፕሮግራም እንዲይዝ ይፈለጋልን?

ሐማስ ይህን ብታደርግ ራሷን ትከስር ነበር። እንዲሁም እምነቱን የሰጣትን ህዝብ እስከመጨረሻው ታጣ ነበር። ምን አልባት ወደ ሚቀጥለው መስመሮች የሚያመራን ሐሳብ ይህ ይሆናል። (ይህ ሃሳብ) ብዙሃኑን ወደ ሐማስ ፕሮግራም ያረባረበውንና የመራውን በመጨረሻም ተገልብጦ የፍልስጤማውያንን የምርጫ ሳጥን የሞላውን ሰበቦች እንመለከታለን።

ሐማስ ለምን አሸነፈ?

በ2006 እአአ ሁሉም በተመለከተው ምርጫ ላይ ህዝቡ እንዲህ ሀማስ ላይ የተረባርበው ብዙ ምክንያቶች አሉ። ከነዚያህ ውስጥ፡-

አንደኛ፡ የኢስላም ሁለንተናዊነት፡-

ሐማስ ለእስልምና ያለው ዕይታ የፍልስጤማውያንን ህዝብ ስቧል። ምንም እንኳ ወታደራዊ፣ ተዋጊና ታጋይ እንቅስቃሴ ቢሆንም በነዚህ ብቻ የተገደበ አይደለም። ሐማስ ህዝቡ ዘንድ በሁሉም ነገር ተዋህዷል (በጤና ጉዳይ፣ በማህበራዊ፣ በዕውቀት ዘርፍ፣ በአገልግሎቶች...)። ሐማስ ልገሳው በፖለቲካና በጂሃድ ብቻ የታጠረ አይደለም። ህዝቡ የሐማስ ልጆች እስልምናን በሁሉም የህይወት ክፍሎቻቸው ሲተገብሩ ተመልክቷል። ፍልስጤማውያን (በሀማስ ልጆች ሰበብ) የእስልምና ሁኔታ ልብን የሚገዛ (የሚማርክ) መሆኑን ተረዱ። እርሱ (እስልምና) ሙሉ የህይወት ጉዳዮችን ስርአት የሚያሲዝ መሆኑን

(ተረዱ)። ***<<ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለአለማት ጌታ ለአላህ ነው>> በል።*** (አንዓም 162)

<u>ሁለተኛ፡ ምርጥ ሚዛናዊነት፡-</u>

ሐማስ ከሌሎች የፍልስጤም ፓርቲዎች ጋር (ምንም እንኳ ግልፅ የሆነ የርዕዮተ ዓለም ልዩነት ቢኖራቸውም) ምርጥ የሆነ ሚዛናዊ ግንኙነት አለው። ይህ ሚዛን በሐማስ መንገድ ላይ አዲስ ወይም ድንገት የሆነ አይደለም። ይልቁንስ ከሰማንያዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ እንደ ኢስላማዊ የትግል እንቅስቃሴ ከተመሰረተ ጀምሮ ሲከተለው የነበረ ቋሚ መንገዱ ነው።

እንዲያውም ሐማስ መንበረ ስልጣኑን ሲረከብ ለተለያዩ ፓሪቲዎች አንድ ሀገራዊ ፓርቲ እንዲሆኑ (ምንም እንኳ ለነርሱ ፈላጊ ባይሆንም፤ ግልፅ ለሆነው የስልጣን ፈተና ቢያጋልጠውም) በጥብቅ (በችክታ) ሲጣራ ነበር። ነገር ግን እነኚህ ፓርቲዎች -የሐማስ

“ስህተተኛ” ብለው የሚያስቡት ሙከራ ገፋፍቷቸው- ሁሉም መጣመሩን አሻፈረን አሉ።

እንዲህም ሆኖ ዛሬም ሐማስ -ለብቻው መንግስት ከመሰረተም በኋላ- እጆቿን በንፁህ ልብ የፍልስጤም ህዝብ ሰቆቃ እንዲቆምና በዋናነት የመሬት ወረራውንና የመብት ጥሰቱን ከህዝቡ ላይ እንዲቆም ለሚያግዝ ሁሉ እንደተዘረጋ አለ።

<u>ሶስተኛ፡ ከፍልስጤማዊ ደም መጠበቁ፡-</u>

ሐማስ ከፍልስጤማዊ ደም ለመራቅ ይጣጣራል። እንዲሁም ጥይትን ወደ ትክክለኛው ዓላማ ወደ ጋራ ጠላት እንዲያነጣጥርና ምንም ያህል ልዩነት ቢኖር ከውስጣዊ ሽኩቻዎችና ግጭቶች በሚችለው አቅም ይርቃል።

እንዲሁም በቀድሞ መንግስት ውስጥ በፍልስጤማውያን ፖሊሶች፥ ልጆቹ ላይ በሚደርስበት

ወከባና እስር (ብዙ ስቃይን ጨምሮ) ሐማስ ልዩ ትዕግስትና ነፍስን መቆጣጠር አሳይቷል።

ፍልስጤማውያን ይህንን ግሩም መንፈስና ለጉዳያቸው (ለዓላማቸው) ትክክለኛ ቀደምትነት ያላቸውን ቅደም ተከተል ሐማስን ለመምረጣቸው ምክንያት መሆኑ አያጠራጥርም።

<u>አራተኛ፡ የራዕያቸው ግልፅነት፡-</u>

የሐማስን ፕሮግራም ልዩ ከሚያደርገው ነገሮች ውስጥ አሁንም ለፍልስጤም ጉዳይና ለጠላቱ ለፅዮናውያን ሃይል የትግል ጉዞ ያለው ግልፅ ራዕይ ነው። የሚታገሉት ለጠላት እንዲት ስንዝር ዕውቅና ሳይሰጡ ሁሉንም በ1948 ሆነ በ1967 እአአ የተወረሩትን ሙሉ ለሙሉ ነፃ ለማድረግ ነው። ሁሉም የፍልስጤም መሬት (ከባህር እስከ ወንዙ) የእስልምና ወቅፍ (Abeyance) ነው። እርሷን ነፃ ማውጣት የትኛውንም ዋጋ ቢያስከፍላቸው በሙስሊሞች ላይ ግዴታ ነው።

አምስተኛ፡ የእጃቸው ንፁህነት፡-

የሐማስ ልጆች (እና ሌሎች በነርሱ አይነት ኢስላማዊ መንገድ የታነፁ) በንፁህ እጆቻቸውና ከህዝብ ገንዘብ እጆቻቸውን በመቆጠባቸው ይለያሉ። እንዲያውም የሐማስ አመራሮች ሁሉም ፍልስጤማዊ ደሞዝተኛ ክፍያውን እስኪወስድ ድረስ የራሳቸውን ደሞዝ ባለመውሰድ ይታወቃሉ። በኢስላማዊ እነፃ ጥላ ስር አልያም በኢስላማዊ መንግስት ስር የሚታየው የመሪና የተመሪ መዋሃድ በየትኛውም መስክ ምሳሌ አይገኝለትም።

ስድስተኛ፡ ፖለቲካዊ ጥበብ፡-

የሐማስ ጉዞ ምንም እንኳ በዙርያቸው ከሚገኙ የዓረብ ሀገራት አካሄድ ቢለይም ድንቅ በሆነ ፖለቲካዊ ጥበብ ከነዚህ የጎረቤት ሀገራት ጋር ጥሩ ግንኙነት መፍጠር ችሏል። እንዳውም አብዝሃኛው የጎረቤት ሀገራት ሃማስ የያዘውን መንገድ የሚፋለሙና የሚያሳድዱ ቢሆንም ሐማስ ግን

በአላህ ፍቃድ ጥሩና ሁለትዮሽ መከባበር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ከተለያዩ ዐረብ ሀገራት ጋር መመስረት ችሏል።

<u>ሰባተኛ፡ አመራሩ በወታደሩ ምሽግ ውስጥ፡-</u>

ፍልስጤማውያን የሐማስ ልጆች ለመስዋእትነት ያላቸውን እሽቅድድም ስለተመለከተና ሁሉንም ኢስላማዊ ምድርን ነፃ ለማድረግ ነፍሶችን ሲገብሩ ሲመለከት ሊመርጣቸው ችሏል። በዚህም መሪ ወይም አለቃ አልተለየም። መስራቹ መሪ ሸይኽ አህመድ ያሲን ተሰውተዋል። ተተኪውም ዶ/ር ዐብዱል ዐዚዝ ረንቲሲ እንዲሁም ሌሎች ብዙ ብዙ የቀደማቸውና የተከተላቸው የፖለቲካና የወታደር አመራሮች አሉ። እንደ ዒስማኢል አቡ ሸነብ፣ ሳላህ ሸሃዳ፣ የህያ ዓያሽ፣ ማህሙድ አቡ ሁኑድ፣ ዓማድ ዓቂል እና...የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የነበረው የዶ/ር ማህሙድ አዝዛሃር መኖርያ ቤት ዒላማ ተደርጎ

እንዲመታ ተደርጎ ነበር። አዝዛሃር የመቁሰል አደጋ፤ ልጁ ደግሞ ሊሰዋ ችሏል።

ፍልስጤማውያን የሐማስ ስሪትን በልዩ ቅርፅ የተሰራ ሆኖ አግኝተውታል። አመራሮቹ ወታደሮቹን በተቀጣጠለና በተፋፋመ ምሽግ ውስጥ ትተው እነርሱ አስተማማኝና ፀጥ ባለ ሀንጻዎች ውስጥ የሚመሸጉ አይደሉም። ይልቁንስ ሁሉም መሪውም ወታደሩም በአላህ መንገድ የሚገኝ ሰማእትነት ውድ ምኞታቸው እንዲያውም ትልቁና ዋናው ምኞታቸው ነው።

ስምንተኛ፦ ቶሎ ማገገም (መላመድ)፦

ሐማስ ብዙ ጊዜ ጉዳት ሲደርስበት ሁሉም ከክስተቱ በኋላ ሚቀጥል አይመስላቸውም ነበር። አማኞች የሀያ ዓያሽና ሰላህ ሸሃዳ ሲሰው ለቀሳም ብርጌድ (የሐማስ ወታደራዊ ክንፍ) ፈርተው ነበር። ነገር ግን እንቅስቃሴዋ (በአላህ ፍቃድ) ቁስሎቿን ቶሎ

ታክማለች፤ ጉዞዋንና ትግሏን ታስቀጥላለች። ከቆይታም በኋላም ቢሆን ምላሹን ትሰጣለች።

ቀናቶች ነጉደው በአንድ ወር ወስጥ ሁለቱ ጀግኖች አህመድ ያሲንና ረንቲሲ ተሰው። ብዙሃኑ ሐማስ መንገዱን በመቀጠሉ ላይ መጥፎ ጥርጣሬን ጠረጠሩ። ነገር ግን በአላህ ፍቃድ በሚገርም ፍጥነት ከጉዳዩ ጋር ቶሎ መላመድና ከአስቸጋሪ ጊዜያቶች ጋር እንዴት መሄድ እንዳለባቸው በሚከተሉት መንገድ ሁሌም ይለያሉ።

እንዲሁም በአመራሩ በትንንሽ ነገሮች መጠቀምን ሁሌም ድንቅ በሆነ ስልት ሲገለገሉበት እናያለን። ሁላችንም ገምተን በማናውቃቸው ትናንሽ ነገሮች ቀሰም ሚሳኤሎችን ሲሰራ ተመልክተናል። እኚህ ሚሳኤሎች -በትናንሽ ነገር ይሰሩ እንጂ- የጠላት (የወረራቸውን) ይዞታዎች በአግባቡ ምትመታ ናት። እንዲሁም ሁሉንም ያስገረመውን ምድር ስር የሚገኙ ዋሻዎችን በመጠቀም የአይሁድ ወታደራዊ ካምፕን

ከስሮቻቸው የማፈንዳት ተልዕኮንና ስራ የምንዘነጋው አይደለም።

ከላይ ባሳለፍናቸው ምክንያቶች ሐማስ ሊመረጥ ችሏል። ከዚህ በፊት የፍልስጤማውያንን እምነት በጂሃድና በወታደራዊ አቅሙ እንዳገኘው ዛሬም በአመራርና በፖለቲካ ዘርፉ እምነታቸውን ሊያገኝ ችሏል። አሁን በቀላሉ ከላይ ያሳለፍናቸው ነጥቦች ህዝቡ በመሰረታዊነት ሐማስን የመረጠበት ያልተፃፈ ፕሮግራሙ ማለት እንችላለን።

ከነዚህ ጉዳዮች አንዱን የተወ በኢስላማዊ ፕሮግራም ላይ ሙሉ ለሙሉ ታማኝነትን ያጣል። ስለዚህ የትኛውም ፍትህ፣ የትኛውም ምክንያት ሐማስን ሙሉዕ ከሆነው ኢስላማዊ ፕሮግራም እንዲተው ሊፈቅድ አይችልም።

<u>ታሪክን በማንበብ...ተስፋን እንሰንቃለን!</u>

የፍልስጤም ወንድሞቻችን በሚያልፉት ከባድ ሁኔታ የዓለም ኋያላን የሐማስ መንግስትን ለመክበብ ሲረባረቡ ነፍሶች ተስፋን ለመቁረጥ ከተቃረቡ ወደ ኋላ መለስ ብለን ከህዝበ ሙስሊሙ ታሪክ እጅግ አስጨናቂ የነበረውን መመልከታችን የግድ ነው። (በታሪካችን እንዳየነው) ሙዕሚኖች የተከበቡበት (የታገቱበት) ሁኔታ በጣም ከባድ፤ ወራሪዎችም ችካላቸውን የተከሉበት ነበር። ከዚህ ሁሉ ጋር ሙዕሚኖች ያለ ድልና ያለሽንፈት ምንም ማድረግ ሳይችሉ ቀርተው አይደለም ከችግሮቻቸው የወጡት። ነገር ግን ከችግሮቻቸው አወጣጣቸው በጌታቸው አሸናፊነትና ኋያልነት ተማምነው፣ በመሪነታቸው አምነው እንዲሁም ጠላቶቻቸውንና ከበስተጀርባዎቻቸው ያሉትን ኋይሎች አሸንፈውና ደምስሰው በድል አድረጊነት ነው (የወጡት)።

-ትምሕርት ከአህዛብ፦

መዲና ላይ በአህዛቦች ከበባው (እገዳው) ሲበረታ ነፍሶች ተጨነቁ "***ዐይኖችም በቃበዙ፣ ልቦችም ለንቃዎች በደረሱ ጊዜ...***" ሙስሊሞች ላይ ብርድ፣ ርሃብ፣ ፍራቻ...ተጨማምረው ተሰበሰቡባቸው። ሁሉንም ቀሳዊ (እንኪን ለማሸነፍና ድል ለማድረግ ቀርቶ) መከላክያና መዳኛ ነገሮችን አጡ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያሉ ረሱል ﷺ ያበስሯቸው ነበር። ብስራቱም ቁረይሽና አጋሮቿ ካደረጉት ከበባ እንደሚወጡ አይደለም። ይልቁንስ አለምን መምራት ነበር። ኢማም አህመድ ከበራእ ኢብን አዚብ እንደዘገቡት ሙስሊሞች ጉድጓድ እየቆፈሩ ሳለ አንድ ድንጋይ ጠነከረባቸው። ረሱል ﷺ ሊያግዟቸው መጡ። **"መፍለጫውን (መጥረቢያውን) ያዙ። ከዚያህም 'በአላህ ስም' ብለው በሀይል መቱት። የድንጋዩ አንድ ሶስተኛ ተሰበረ። ከዚያህም 'አላህ ወአክበር! የሻም ቁልፍ ተሰጠኝ። በአላህ ይሁንብኝ በዚህ ቦታዬ ላይ ሆኜ ቀያይ**

ቤተመንግስቶቿ ይታየኛል’ አሉ። ከዚያህም ‘በአላህ ስም’ ብለው ለሁለተኛ ጊዜ መቱት። የድንጋዩ አንድ ሶስተኛ ተሰበረ። ‘ከዚያህም አላህ ወአክበር! የፋርስ ቁልፍ ተሰጠኝ። በአላህ ይሁንብኝ እዚሁ ቦታዬ ላይ ሆኜ ከተሞቿንና ነጩ ቤተመንግስትን እየተመለከትኩ ነው’ አሉ። ከዚያህም ‘በአላህ ስም’ ብለው ድንጋዩን በኋይል ሲመቱት የቀረው አለት ተሰባበረ። ‘አላህ ወአክበር! የየመን ቁልፍ ተሰጠኝ። በአላህ ይሁንብኝ! ከዚሁ ቦታዬ ላይ ሆኜ የሰንዓ በሮች ይታዩኛል’ አሉ” ይህን ብስራት (የተጨባጩን መራራነት የተመለከተ) ዕውነተኛ የሙዕሚኖች ልብና አዕምሮ እንጂ ሊሸከመው አይችልም። መናፍቃን ግን እንዲህ አሉ **“...አላህና መልዕክተኛው ማታለልን እንጂ ሌላን አልቀጠሩንም”** (አህዛብ 12)

አሁን አስብ እስቲ! የፍልስጤም ጀግና የሆኑትን ታጋይ ሙስሊሞችን አሁን ካሉበት ከባድ ጊዜ እንደሚወጡ ብቻ አይደለም የሚያበስራቸው። ይልቁንስ ምድርን

በመቆጣጠርና ዐለምን በመምራት ነው እያበሰራቸው ያለው።

ይህ ብዙዎች ዘንድ ከንቱ ምኞትና ቅዠት ነው። ነገር ግን ዕውነተኛ ምዕመን ዘንድ አንዳች ጥርጥር የሌለው ዕውነት ነው ***"አላህ እነዚያን ከእናንተ ያመኑትንና መልካም ስራዎችን የሰሩትን እነዚያን ከእነሱ በፊት የነበሩትን እንደተካ በምድር ላይ በእርግጥ ሊተካቸው፣ ለእነሱም ያንን የወደደላቸውን ሃይማኖታቸውን ሊያደላድልላቸው፣ ከፍርሃታቸውም በኋላ ጸጥታን ሊለውጥላቸው ተስፋን ቃል ሰጥቷቸዋል። በእኔ ምንንም የማያጋሩ ኾነው ይገዙኛል።..."*** (ኑር 55)

ይህንን የሚጠራጠር ሰው ኢማኑን ተመላልሶ ይፈትሽ ***"አላህ (መልዕክተኛውን) በቅርቢቱም በመጨረሻይቱም ዓለም አይረዳውም ብሎ የሚያስብ ሰው ገመድን ወደ ሰማይ ይዘርጋ። ከዚያም (ትንፋሹ እስኪቆረጥ) ይታነቅ። ተንኮሉ***

የሚያስቆጨውን ነገር ያስወግድለት እንደሆነም ይመልከት።" (ሐጅ 15)

<u>-በመስቀላውያን ታሪክ ውስጥ ትምህርት አለ፦</u>

ሙስሊሞች ሰማንያ አመት የሚጠጋው አይሁድ ፍልስጤማውያን ላይ ያደረሰው ወረራ ካስረዘሙት (ረዥም ከመሰላቸው) መስቀለኞች ካሁን በፊት የፍልስጤምን መሬት ለሁለት መቶ አመት ወረውታል። (መስቀለኞቹ) ልክ እንደ አይሁዶቹ ለመስፈር ነው የመጡት። ማለትም ወታደሮች ብቻ አይደለም የመጡት። ይልቁንስ ቤተሰቦቻቸውንና ንብርቶቻቸውን ነው ይዘው የመጡት። የፍልስጤም ምድር ላይ የመስቀለኞች ትውልድ ተፈራረቁባቸው። አላህ ድሉን እስኪፅፍላቸው ድረስ ረዥም ጊዜ ከመታገል ዕውነተኞቹ ሙስሊሞች ተስፋ አልቆረጡም ነበር።

አያቶቻችን ከሁለት መቶ የወረራ አመታት በኋላ ነፃ ካደረጓት እኛ ደግሞ ዛሬ በአላህ ፍቃድና እገዛ እሷን

ነፃ ማድረግና እርሷን ማስመለስ ላይ ቻይና ቅርብ ነን።

- **<u>ሐማስ ትላንት እና ዛሬ</u>**

ሩቅ የሆነው የዑመተል ኢስላም ታሪክ ሕያው የሆነ የአላህን እርዳታና ቅርብ የሆነ መከፈት ተስፋ የማይዘራብን ከሆነ ትላንት ሐማስ ካለፈባቸው ለምዕመናን ቀልብ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ተስፋን የሚሰጥን በአላህ ፍቃድ የድል ብስራቶችን የሚጨምሩትን ጉዞ በአላህ ፍቃድ እንመለከታለን።

በ1992 እአአ ከ400 በላይ የሐማስ አመራሮች ወደ "መርጅ አል ዙሁር" (ሊባኖስ ጋር የሚያዋስናት ድንበር) ተገፍተው (ተባረው) ነበር። ያኔ ከተባረሩት ውስጥ "ኢስማዒል ሀኒያ"፣ "ማህሙድ ዘሃር" እና ሌሎችም ለአንድ አመት ያክል እኚህ ጀግኖች ከባድና አስጨናቂ ችግር ውስጥ ነበሩ። እንዲሁም መራራ ብቸኝነትና መነጠልን አስተናግደዋል። ከሀገር መሰረታዊ የሆኑ ሰብአዊ መብትን እንኳ በጣሰ

ሁኔታና ያለ በቂ ልብስ በቀዝቃዛ የአየር ፀባይ ሲባረሩና ሲሳሸገሩ ስንመለከት ልቦች በሀዘን ደምተው ነበር። ምን አልባት እንዳንዶች (ከሁኔታው ከባድነት) እኒህ ሰዎች አይደለም ጠቅላይ ሚንስቴርና የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ይሆናሉ ብሎ ሊያስብ ይቅርና ወደ ቤተሰቦቻቸው በሰላም የሚመለሱ መኾናቸውን የጠረጠሩ ነበሩ።

ቀናቶች እየነጎዱ በሐማስ እንቅስቃሴ ላይ ዱላው ተፈራረቀባቸው። 2004 እአአ መጣና አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሁለት ጀግኖች አህመድ ያሲንና ዶር ዐብዱል ዐዚዝ ረንቲሲ ሰማእት ሆኑ። ብዙዎች ዘንድ ሐማስ ዳግም ህያው ሆኖ መቀጠሉ ላይ አንፀበራቂ ተስፋ ጠፍቶ ነበር። አንድም ሰው ይህ ተሰዳጅ እንቅስቃሴ ከሁለት አመት በኋላ ለብቻዋ ተመርጣ መንግስት ትመሰርታለች ብሎ የጠረጠረ አልነበረም። ነገር ግን አላህ ለባሮቹ ድንቅ ከሆነው ውሳኔው ሌላኛውን ጎን ሊገልጥላቸውና (ለባሮቹ ያለውን) አስደናቂ አስተናባሪነት ሊያሳያቸው ፈለገ፦

“(ሙሐመድ ሆይ!) በል፦ <<የንግስና ባለቤት የኾንክ አላህ ሆይ! ለምትሻው ሰው ንግስናን ትሰጣለህ። ከምትሻውም ሰው ንግስናን ትገፍፋለህ። የምትሻውንም ሰው ታልቃለህ። የምትሻውንም ሰው ታዋርዳለህ። መልካም ነገር ሁሉ በእጅህ (በችሎታህ) ነው፤ አንተ በነገሩ ሁሉ ቻይ ነህና።>>” (አለ ዒምራን 26)

<u>አንተና ፍልስጤም</u>

ከተጫበጩ ትግበራ ምንም ሂሳብ የሌለው በመልካም እሳቤ ብቻ መብቃቃት...ባለቤቱ ለሚፈልገው ግብ ሊያደርሰው አይችልም።

- ጀነት ለመግባትና ለርሷ የተገባ ለመሆን ተግባርና ትግል ግዴታ አስፈላጊ ነው።
- ፍልስጤማውያን ወንድሞቻችን እየገጠማቸው ላለው ነገር ተራ የስሜት መነካት ብቻ የረባ ጥቅም የለውም። ተራ የድልና የመደላደል ምኞትም እንዲሁ አይጠቅማቸውም። ይህ ስሜት ወይም ምኞት ፍልስጤማውያን ወንድሞቻችን ዕውን የሆነውን ድል ለማምጣት አይበቃም። ግዴታ ስራ (ተግባር)፣ መስዋእትነትና ያለ ስስት መስጠትን ይጠይቃል። ምንም እንኳ እነሱ (ፍልስጤማውያን) በሚሰጡት ልክ ደምና

ነፍስ ባይሆንም አሁን ባለው ሁኔታ በሚቻለው በትንሿ ነገር መሳተፍህ ይበቃል።

ስለዚህ አሁን ላይ ቆም ብለን በየትኛውም ሁኔታ ሊታጡ የማይገቡና ከነርሱ መውረድ የማይቻልባቸውን የተወሰኑ ሃላፊነቶቻችንን እንመለከታለን።

<u>አንደኛ፡ ጉዳዩን ማንቀሳቀስ፡-</u>

በዙርያችን ከሚገኙ ሙስሊምና ሙስሊም ያልሆኑ ወንድሞች ልብ ውስጥ ትክክለኛ የሆነውን የፍልስጤምን ጉዳይ መቀስቀስና እንዲሁም እርሷን በመርዳት ላይ ቁርጠኝነትን ማምጣት ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል። ባለፉት ገፆች ላይ ያሳለፍናቸውን አረዳዶች ራዕዩ ግልፅ እስኪሆንና ሰዎች ይህን ጉዳይ ለመርዳት የተረዳና አሻራ ያለው እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ በሙስሊሙ አዕምሮ ላይ ማሰራጨት የግድ ነው። ዐለምን የጉዳያችን ፍትሓዊነት ለማስተዋወቅና

የሙስሊሞችን ቁርጠኝነትን (ፍላጎት) ለመቀስቀስ ማህበራዊ ሚድያዎችን በመልካም ለመጠቀም የፈለገ እጅግ ብዙ ናቸው። ሩቅ ያለን ሙስሊም ስሜትና ቁርጠኝነት በኢሜል መልዕክቶች (አልያም መሰል መተግበርያዎች)፣ ለዚሁ ጉዳይ በተሰሩ ዌብሳይቶች፣ ከሳተላይት በሚመነጩ ፕሮግራሞች ማንቃትና ማንቀሳቀስ ይቻላል። እነዚህ ነገሮች አንተ ለብቻህን መተግበር ማትችለውን ያሳኩልሃል። ይህ ሁሉ በአንተ የመልካም ምንዳ ሚዛንህ ላይ ይቀመጥልሃል።

ሁልግዜና በተደጋጋሚ የፍልስጤምን ጉዳይ ማሰራጨት፣ የጉዳዩን ኢስላማዊነት ማወጅና በፍልስጤም ጉዳይና በሙስሊሞች ልብና አእምሮ መካከል (በትክክለኛው ቅርፅ) የማይበጠስ ጠንካራ ገመድ መዘርጋት ሌላኛዋ አንደሉስ እንዳትሆን እጅጉኑ አስፈላጊ ነው።

ሁለተኛ፡ በገንዘብ መታገል፡-

(ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን) ከሁሉም ኡማ ላይ ለመከላከል በፍልስጤማውያን ወንድሞቻችን ላይ ነፍስ፣ ገንዘብን...መስጠት ግዴታ ከሆነባቸው፥ አላህ ከመወረር፣ ከመፈናቀል፣ በተከታታይ ደሞዝ ከመታገድ ...ሰላም ያደረገው አንድ ሙስሊም ግለሰብ ወንድሞቻችን ፅናት ይሆናቸው ዘንድ እዚህ ገፅ ላይ ተብራርቶ የማያልቀውን መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ማሟያ ይሆናቸውን ዘንድ በገንዘቡ ጂሃድ ማድረግ አለበት። ለምሳሌ ያክል በሆስፒታሎች የመድሃኒቶች እጥረት (ማለቅ)ና ሐማስ ስልጣኑን ቁልፍ ከተረከበ ጀምሮ (በበጀት እጥረት) ለሺዎች ወርሃዊ ደሞዛቸውን መክፈል አለመቻሉን መጥቀስ ይቻላል። እንግዲህ ወደ ፍልስጤም የሚገቡ መሰረታዊ መገልገያዎች (እንደ ነዳጅ) ገንዘብ ባለመኖሩ ሚጠበቅባቸውን በጊዜ ባለመክፈላቸው ከኢስራኤል የሚደርስባቸውን (የማቆም) ማስፈራርያ ሳይጨምር ነው።

ከላይ ያሳለፍናቸው በሞሉ (ከብዙ አስደንጋጭ ሁኔታዎች ጥቂቱ) ሐገራት የፍልስጤም ህዝብ ሐማስን በመምረጡ እርዳታ በማቋረጥ ያደመባቸው ነው። ምዕራቡ ዓለም ፍልስጤምን ቢከብና ቢያብርባት እኛ ግዴታችን የሆነብንን "በገንዘብ ጂሃድ" ማድረግን ችላ እንላለን? ይቺህን ሸሪዓዊ ግዴታን ሁላችንንም (አንድ በአንድ) አላህ ፊት እርሷን በመተግበራችን አልያም ከርሷ በማጉደላችን ምንጠየቅበት ነው።

ከኛ ውስጥ ማንኛውም ሰው ለፍልስጤም የሚያደርገውን ነገር አሳንሶ አይመልከት። አንድ የሐማስ አመራር በግብፅ ህዝብ (የግብፅ ህዝብ ከሚያልፈበት ከባድ የኢኮኖሚ ጫና ጋር) ምሳሌ ሰጥቶ ነበር። እያንዳንዱ ግብፃዊ በወር 1 ጂኔ ቢያዋጣ በወር 70,000,000 ጂኔ የሚጠጋ ገንዘብ ይሰበሰብ ነበር። ይኼ ገንዘብ የፍልስጤም ባለስልጣን እንዳለው የፍልስጤም አንድ አስረኛ በጀት ነው።

አየህን?! ሁሉም ግብፃዊ ከገንዘቡ በአላህ መንገድ ላይ (በወር አስር ጂኔ) ለፍልስጤም ማውጣት ይከብደዋልን? በዚህ መዋጮዋቸው ግብፃውያን ለብቻቸው (ከሌሎች ሙስሊሙ ማህበረስብና ሌሎችም ከሚያዋጡት ገንዘብ ውጪ) የሐማስ መንግስትን በጀት ሙሉ ለሙሉ መደጎም ይችላሉ።

(አንተስ የኢትዮጵያ ሙስሊም ሆይ! አንተ ሀምሳ ሚልየንን የተሻገርከው ሙስሊም ህዝብ ሆይ! አየህን?! አያንዳንዱ ሙስሊም በወር ለፍልስጤም ወንድሞቹ ሀያ ብር ቁጭ ቢያደርግ ምን እንደሚፈጠር? ለወንድሞችህ በወር 1 ቢልየን ብር መደጎም ትችላለህ። የዳሩል ሒጅረተይን ምድር ሆይ! በገንዘብ ጂሃድ ለፍልስጤም የምንዋጋለት ሰዓት አልደረሰምን? - ተርጓሚው)

ለእያንዳንዱ የቤተሰብህ አባላት 10 ጂኔ ማውጣት ብዙ ከመሰልህና ዐይንህ ላይ ከገዘፈብህ (በአማካይ የግብፅ ቤተሰብ 50 ጂኔ ማለት ነው) ቤተሰብህ ሌላ

ቤተሰብ እንደጨመሩ አስብ። አላህ ለከለከለን ነገር ምናወጣውን ነገር ትተን እጅግ ቅንጡ (ትርፍ) ለሆኑ ነገሮች ብቻ ብዙ ገንዘብ እንደምናወጣ ግልፅ ነው። ከሀራም ጉዳይ የሲጋራን ነገር ላንሳ። አንድ አጫሽ እስቲ ራሱን ይጠይቅ። ወደ ቤተሰቡ ወጪና ለኑሮ አስፈላጊ ነገሮች ሳይመለከት ራሱን በሲጋራ ለማጥፋት በወር ስንት ያወጣል? (በዚህ ገንዘብ) ለፍልስጤም ጉዳይ ጂሃድ ማድረግ፣ ከሲጋራ ሱስ ለመውጣት እንደ አጋጣሚና መንገድ አድርጎ ለመያዝ እንዲሁም አዕምሮን ለመጠበቅና የምፅዋት አስፈላጊነት ራሱ ላይ ከፍ ለማድረግ አይጠቀመውምን? ቲርሚዚ ሳሂህ በሆነ ሀዲስ እንደዘገቡት አንድ ባርያ የዓለማት ጌታ ፊት **“ገንዘቡን ከየት እንዳመጣውና ምን ላይ እንዳወጣው?”** እስኪጠየቅ ድረስ እግሩ እንደማይንቀሳቀስ አያውቅምን?

ሁላችንም አሁን ወረቀትና እስኪብርቶ እንያዝ። ከዚያህም ለፍልስጤም በወር ስንት እንደምንወጣ

እንወስን። ከዚያህም ነፍሱን በፃፈው ነገር ላይ ያስገድድ። ከዚያም በዚህ ላይ ይዘውትር (ትንሽ ነገር ቢሆንም (ዘውታሪነት ያለው ነገር) አላህ ዘንድ ተወዳጅ ነው)። ገንዘብ እስኪሰበሰብልኝ ብለህ አታሳልፈው አልያም ደግሞ የወሩን መጨረሻ እየጠበቅህ መክፈል እስከማትችል ድረስም አትቆይ። ሸይጣን አይተውህም። እርሱን በማሸነፍ ላይ ተቻኮል። ጌታህ ዘንድ ሚዛንህን ክቡድ አድርገው።

ማንም ሰው ፍልስጤም አሁን ባለችበት ከበባና ሀገራቶች የፍልስጤም ምድር ላይ ገንዘብ እንዳይገባ በማገዳቸው ገንዘቡ ለእነርሱ አይደርስም ብሎ ምክንያት አያድርግ። በአላህ ይሁንብኝ! በኢማናችን ሀይል፣ ለአላህ መንገድ በዚህ ገንዘብ በርሱ መንገድ እንደምንታገል ባለን ዕውነተኛነትና ኢኽላስ ይደርሳል። ***እነዚያም በእኛ መንገድ የታገሉ መንገዳችንን በእርግጥ እንመራቸዋለን። አላህም በእርግጥ ከበጎ ሰሪዎች ጋር ነው።*** (አንከቡት 69)

እዚህ ጋር ግዴታ ከፍ ያለ ቆራጥነት መኖር አለበት። ግዴታ ውዳቂ ከሆነው ዱንያ የአላህን ምንዳ የሚታስበልጥ ነፍስና ልብ ያስፈልጋል። ግዴታ ከአላህ ጋር ለመነገድ ምትጓጓ ነፍስ መኖር አለባት። ግዴታ!!

አቡበክር አስሲዲቅ (ረዐ) በዚያህ ከባድ ወቅት ሙሉ ንብረቱን ሰጠ። ዑመር ኢብኑል ኸጣብ (ረዐ) ግማሽ ንብረቱን ለገሰ። ዑስማን ኢብኑ ዓፋን (ረዐ) አንድ ተጓዥ ከሚያስፈልገው ሙሉ ስንቅ ጋር በመቶዎች የሚቆጠሩ መጓጓዣ አዘጋጀ። የዕውነተኛ ሙዕሚን ነፍሶች ትንሹንም ትልቁንም ለገሱ።

- ከኛ ውስጥ ዑስማን ኢብኑ ዐፋን ማን ነው?
- ከኛ ውስጥ አቡበክር አስሲዲቅ ማን ነው? ማን ነው ዑመር ኢብኑል ኸጣብ? ማን ነው ዐብዱል ራህማን ኢብኑ ዐውፍ?
- ከኛ ውስጥ ማን ነው የከባድ ወቅት ወታደር የሚያዘጋጅ?
- ማን ነው ከኛ ውስጥ ጀነትን የሚገዛ?

ሶስተኛ፡ አድማ (አለመግዛት) Boycott:-

የሙስሊሞች ቆራጥነት አይሁድን፣ አሜሪካን፣ ኢንግሊዝን አድማ በማድረግ ፅናት ተስፎቸው መመልከት ያሳዝናል። ምንም እንኳ እኚህ ሀገሮች በፍልስጤም፣ በሚራቅ፣ በአፍጋኒስታን... ላይ ወንጀሎቻቸው ቢቀጥልም ሙስሊሞች ግን (አላህ ያዘነለት ሲቀር) ዛሬም ምርቶቻቸውን ለመግዛት ሲሸቀዳደሙ ይስተዋላል።

የሙስሊሙ ስብእና ጠዋት ማታ ወንድሞቹን ከሚያርዱት ጋር እንዴት መፎካከርና መስራት እንደቻለ ግራ ይገባኛል። እንዲያው አድማ ለማድረግ ሸሪዓዊ ግዴታነት ባይኖር እንኳ ነፍሶቻቸው ውስጥ ንጹህ ደምን ቀን ከሌሊት የሚያፈስ ላይ ግዴታ የሚያደርግ ሰብአዊነት የለምን?

ብዙዎች ረሱልን ﷺ የሚያነውር ምስል በወጣ ጊዜ ዴንማርክ ላይ አድማ ለማድረግ ተቻክለውና ጓግተው ነበር። በሁሉም መተግበርያዎች ላይ (አድማ

የተደረገባቸው ምርቶች) ዝርዝር ተሰራጭቶ ነበር። እጠይቃለሁ! የዴንማርክ ምርቶች ለአብዝሃኛው ሙስሊም የንግድ ሂደት ላይ ምን ያክል ቦታ አላቸው (ምን ያክል ተጠቃሚ አላቸው? አስፈላጊነታቸውስ?)? የሚገርመው ሙስሊም ግለሰብ አልያም ሙስሊም ቤት በየቀኑ ሊጠቀመው የሚችል ሚዛን የሚኖረው የዴንማርክ ምርት አይገኝም።

ትክክለኛውና ከባዱ ፈተና ገበያችንን ወረው ትንሽም ሆነ ትልቅ ሙሉ ህይወታችንን ሸፍኖ የሚገኙትን የአሜሪካ አልያም የኢንግሊዝ (ወይም የአይሁድ) ምርቶች ላይ አድማ እንዲደረግ ሲነገርና ስንተገብረው ነው። የዚህ አይነት አድማ (Boycott) ዕውነተኞች ካልሆኑ በቀር ታግሰው ሊተገብሩት አይችሉም።

- **<u>ቢድዓ ሳይሆን ሱንና!!</u>**

እጅግ ከሚገርመውና ከሚደንቀው ነገር የአሜሪካንና የኢስራኤልን ምርቶች አድማ ማድረግን በሸሪዓ

መሰረት የሌላት ፈጠራ (ቢድዓ) ያደረጉትን ስትመለከት ነው።

በአላህ ይሁንብኝ! ግልፅ ውድቀት ማለት ይኼ ነው። ሙስሊም እንዴት የዚህ አይነት አመለካከት ሊኖረው እንዴትስ የዚህ አይነት እይታ ሊኖረው ይችላል? አድማ ማለት እኮ በፈለከው ጊዜ ምትተገብረውና በፈለከው ሰዓት ምትተወው የተፈቀደ ተግባር (ሙባህ) አይደለም። ነብያዊ ሱንና እንጂ። ወደ አላህ የምትቃረብበት ዒባዳ ነው። ከነብዩ ﷺ ሱንና ማስረጃን የፈለገ፦

በኒ ሐኒፋዎች "የማማ" ሚባል ስፍራ ውስጥ "ረይፍ መካ" (ረይፍ ማለት ከከተማው ወጣ ብሎ የሚገኝ እርሻ የሚበዛበት ቦታ ነው። ረይፍ መካ የተባለችበትም ምክንያት ለመካ ነዋሪዎች ከምታቀርበው መብልና ጥራጥሬ የተነሳ የመካ እርሻ መሬት ለመባል በቅታ ነበር) ተብላ የምትጠራ ስፍራ ሰፍረው ነበር። በሰባተኛው ዓመተ ሒጅራ ላይ የበኒ

ሐኒፋ ዓለቃ የነበረው “ሱማማ ኢብኑ አሳል” ሰለመ። ከዚያህም ለዑምራ መካ መጣ። የቁረይሽ አለቆች ፊት “... በአላህ ይሁንብኝ አይደለም! ከየማማ ረሱል ﷺ እስኪፈቅዱ ድረስ አንዲት ፍሬ ጥራጥሬ አታገኙም” ሲል በመኻላ ተናግሯል።

ምንም እንኳ መካ ለሱማማና ለህዝቦቹ የነቃ የገበያ ቦታና ያለምንም ጥርጥር ብዙ ትርፍ የሚያገኙባት ቦታ ብትሆንም ሱማማ (ረዐ) አላህንና መልዕክተኛውን ﷺ ከሚዋጋ ጋር (ምንም እንኳ የሁደይቢያ ስምምነት ወቅት ቢሆንም እንኳ) መሻሻጥን አላሰበም።

በይሃቂ (ረ) ሱነን ላይ እንደዘገበው ሱማማ ቁረይሽ ላይ አድማውን አረዘመው **“ቁረይሽ (ሁኔታው) ከበዳት (አስጨነቃት)። ወደ ረሱል ﷺ በዝምድናቸው እየጠየቁቸው ወደ ሱማማ መብሉን እንዲተውላቸው (እንዲልክላቸው) እንዲጽፉለት ጠየቁቸው... ረሱልም ﷺ እንዲያህ አደረጉ።”**

ረሱል ﷺ ሱማማ ረዐ ቁረይሽ ላይ ያደመው አድማ ኋጢአት ቢሆን ኖሮ በከለከሉትና በኮነኑት ነበር። ነገር ግን እሳቸው ﷺ ለቁረይሽ በማዘናቸው እንዲቀጥል አልፈለጉም። ሱማማ ረዐ አድማውን እንዲተው አዘዙት። መጀመርያ ላይ ይህንን ነገር እንዲተው ዝም ማለታቸው ተግባሩን ማፅደቃቸው ነው። ምክንያቱም የዕውቀት ባለቤቶች እንደገለፁት ሱንና ማለት ከረሱል ﷺ የተገኘ ንግግራቸው፣ ተግባራቸው፣ ያፀደቁት ነገር...ነው።

ስለዚህ አድማ አድማ ከፈለግን ምንሰራው ካልፈለግን ምንተወው (ሙባህ) አይደለም። ይልቁንስ ነብያዊ ሱንና ነው። ዑማው (በመሳርያ መታገል ካልቻለ) ጣዖቶችን የሚጋፈጥበትና እንዲሁም ጠላት ክብሯ ላይ እንዳይረማመድ ልጓም ማድረጊያ ነው።

እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ማለትም ለዑማው ያለው ሙሉ ወዳጅነት የታየበት፣ ለዲኑ ቅድሚያ መስጠት ላለበት ነገር በአግባቡ በተረዳው በሰሃቢዩ ሱማማ

ኢብኑ አሳል (ረዐ) እና ሁለተኛው የአሜሪካንና የኢስራኤልን ምርቶችን ለጣፋጭ ምግብ፣ ለለመደው መጠጥ አልያም ለጫማና ለልብስ ሲል በኡመቱ አጀንዳና በወንድሞቹ ደም እየተላሳለሰ ሚጠቀም አለ። ከነዚህ ከወደዳቸው ምርቶች እንዲቆጠብ ከነገርከው እነዚህን ምርቶች መተው (በሁኔታው) የዐለም ፍፃሜ እንደሆነ አድርጎ እንዲሰማህ ያደርጋል።

ከትንሽ ቆይታ በፊት እንዳነሳነው ጉዳዩ ከሸሪዓ አስፈላጊነት ብቻ የተገናኘ አይደለም። ይልቁንስ ዛሬ አንድ ሙስሊም ዘንድ የሚገኘውን ጥልቅ ሰብአዊነት ማሳያ እንዲሁም በደም ስራቸው የሚዘዋወረውን የፈላ ደም ማሳያ ነው። የምለው ነገር ግልፅ ይሆን ዘንድ አንድ ምሳሌ ልስጥ፡-

ቤትህ ውስጥ ነው ያለኸው እንበል። ከዚያህ ጎረቤትህ (ሙስሊም ቢሆን እንኳ) ወዳንተ ቤት ድንገት ገባ። ከዚያህ በሚስትህና በልጆችህ ፊት በስድብና በምት ድንበር አለፈብህ። አንተ ደግሞ በስድብም ሆነ በሌላ

ምላሹን ለመስጠት አልቻልክም። እንዲህ በተደረክበት ዕለት -እንዲህ ያደረገህ ጎረቤት ነጋዴ ቢሆን- ከርሱ ለእራት የሚሆንህን ነገር ለመግዛት እሺ ትልሃለችን?

ከርሱ ባለመሸመትህና ልጆችህ ከርሱ እንዳይገዙ በመከልከልህ (ወይንም ከጎረቤት ባለመግዛት ሱናን በመቃረንህ) አንድ ሰው ቢሆን እንኳ ሚታዘብህ፤ ሚቃወምህ ይኖራልን??

እስቲ ደግሞ ጎረቤትህ ሙስሊም ያልሆነ ሰው አድርገህ አስብ። ቤትህ እያለህ ወዳንተ ገባ። ልጆችህንና ሚስትህን ፊት ለፊትህ አረዳቸው። አዋረደህ...ንብረትህን ዘረፈ። ከዚያህም አልበቃ ብሎት ከቤትህ አስወጥቶህ እርሱ ሰፈረበት። በአንድ ግዜ ራስህን ጎዳና ላይ አገኘኸው። አንተ ደግሞ ለሆነ ሰበብ ለተደረገብህ ነገር ምላሽ መስጠት (መበቀል) እና ሀቅህን ማስመለስ አትችልም። በዚህ ሁኔታ ጎዳና ላይ እየተዘዋወርክ ርሃብ ያዘህ። ይህን ሁሉ ያደረገብህ

ሰው ዘንድ ስራው ቦታ ሄደህ ርሃብህን የሚያስታግስ ነገር ትሸምታለህን? ዕውን አንድ ባለአዕምሮ ይህን ይቀበላልን?

ዛሬ የአይሁድን፣ የአሜሪካንና የኢንግሊዝን ምርቶች እያሳደዱ መግዛታችን ትርጉሙ ፍልስጤም ያሉትን ዕውን ወንድሞቻችን አድርገን አናስባቸውም ማለት ነው። እንዲሁም ከነርሱ ጋር አንድ የሚያደርገንን የእምነት ግንኙነት እኛ ጋር ስሜት የለውም ማለት ነው። ከነርሱ ጋር በአንድ መፅሐፍ ያለንን አንድነት፣ ወደ አንድ አቅጣጫ ያለንን ቂብላነት፣ ወደ አንድ አምላክ ጎንበስ ማለታችንን አልቀመስነውም ማለት ነው።

ይህን ሁሉ ግንኙነቶች የቀመሰ ጦርነቱ በኛና በነርሱ መካከል በተፋፋመበት ወቅት ከነርሱ (ከጠላቶቻችን) ጋር ሊገዛና ሊሸጥ አይቻለውም።

አንዳንድ ምርቶች ምትክ ስለሌላቸው (ከምርታማነትና ከቴክኖሎጂ ወደ ኋላ በመቅረታችን)

ከነሱ ለመግዛት ምንገደዳቸው እንዳሉ አውቃለሁ። ነገር ግን የዚህ አይነት ምርቶች (ምትክ የሌላቸው) ከጠላቶቻችን ከምንገዛቸው እጅግ በጣም ትንሽ ፐርሰንት ቢሆኑ ነው። እንደ አጠቃላይ አብዛኛዎቹ እጅግ አስፈላጊ ውስጥ አይገቡም። እንዳውም አስፈላጊ ጋር ራሱ አይደርሱም።

አንዳንዶች የአድማ ጥቅም የጠላት ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰው ጫና ያልታያቸው ኡማው እርሷ ላይ ተረባርቦ ያደመባትን ዴንማርክን ሁሉም ተመልክቷል። ስለዚህ የሙስሊሞችን ደም፣ ክብርና መኖርያ ቀንና ለሊት-ማፍሰስና ማፍረስ- የተፈቀደ ያደረጉትን አድማ ማድረግ እጅግ የተገባ ነው።

<u>አራተኛ፡ ዱዓ፡-</u>

ዱዓ በፍልስጤም ጉዳይ ላይ ትንሽ አልያም ተራ ነገር አይደለም። ወይም ደግሞ ስንፈልግ የምናደርገውና የምንተወው የምርጫ ጉዳይም አይደለም። ዱዓ ከድል መሰረታዊ ማዕዘናት ውስጥ አንዱ ነው። ለዲን

ምኞት (መደላደል) የተረጋገጠ ሰበብ ነው። ረሱል ﷺ ዱዓን በፍፁም አልተውትም። የፈለገ ምላሹ ቢቆይ፣ የፈለገ መንገዱ ቢረዝም፣ የፈለገ ጉዳዩ ቢተልቅ (ቢከብድ) አንድም ቀን አልሰለቻቸውም። እሳቸው ﷺ በአስቸጋሪና በከባድ ጊዜ ዱዓ፣ ልመና፣ ኹሹዕ ይበልጥ ይተገብራሉ። እንዲሁም (በአስቸጋሪና ከባድ ጊዜ) ይበልጥ ወደ ጌታቸው ይቀርባሉ፣ ወደርሱ ይሸሻሉ፣ እርዳታውን ይጠይቃሉ፣ እገዛውን ይሻሉ። ይህንን በበድር፣ በኡሁድ፣ በአህዛብና በሌሎች (ከባድ) ቀኖቻቸው ይበልጥ ተመልክተናል።

ፍልስጤም የማይቋረጥ ዱዓ፣ የማይቆም ልመና ትሻለች...

- ወንድሞችህን የሚደበድቡት የአይሁድ የጦር አውሮፕላኖች በዱዓህ ሰበብ ድብደባዋ ቢቆምስ አንተ ምን አሳወቀህ?

- አይሁዶች በምሽት የሚያሴሩት ዕቅዳቸው በአንተ ዱዓ ሰበብ ቢከሽፍስ ምን አሳወቀህ?
- የፍልስጤም ወጣት የሚወረውራት ድንጋይ ወይም የሚቶክሳት ጥይት በአንተ ዱዓ ሰበብ ሚላማዋን ብትመታስ ምን አሳወቀህ?

ቀንና ለሊት የማይቋረጥ እንዲሁም ችክታ ያለበት ሰፊ ዱዓእ የግድ ነው...

- ዱዓ በቁኑታችን በሱጁዳችን
- ምላሹን እርግጠኛ የሆንበት ዱዓእ
- ችኮላም ሆነ ተስፋ መቁረጥ የሌለው ዱዓ
- ከልባችን ወደ አላህ በመተናነስና በመሰበር የምናደርገው ዱዓእ
- ሐላል የሆነ ገንዘብ ብቻ ከሚያድኑ፣ ምርጥ ወቅቶችን ከሚጠባበቁ፣ የተከበሩ ሁኔታዎችን ከሚለዩ ምዕመናን የሚወጣ ዱዓ

- ድቅድቅ ባለ ለሊትና ከፈጅር በፊት የሚደረግ ዱዓ
- ቤተሰቦች፣ የስራ ባልደረቦች፣ በየመስጂዶች ተሰባስበው የሚያደርጉት ዱዓ ያስፈልገናል።

<u>አምስተኛ፡ ወደ አላህ መመለስ፡-</u>

አምላካችን አላህ የፍልስጤምን ጉዳይ የኡማው ጥልቅ እምነት መፈተሻ አድርጎታል። ሙስሊሞች ከሀይማኖታቸው ከራቁ፣ ማንነታቸውን ከዘነጉ፣ የጌታቸውን ህግ ካልተከተሉ ፍልስጤም በወራሪ ቅርጫት ውስጥ ትወድቃለች። ሙስሊሞች ወደ ሐይማኖታቸው ከተመለሱ የጌታቸውን ህግና የመልዕከተኛቸውን ﷺ መንገድ ከያዙ ወደ ሙስሊሞች እጅ ትገባለች። ወራሪዎች ላይ ታጋዮች በበዙ ጊዜ፤ እንዲሁም ትግል፣ ውጊያ፣ ሀይል...ከበረታ የኢማን ጊዜ ነው። ነገር ግን እጅ መስጠትና ማጎብደድ

ከታየ ይህ ከሙስሊሞች ህይወት ላይ ሐይማኖት እንደጠፋ ማሳያ ነው።

ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ወደ አላህ መመለስ ግዴታ ነው። ሙስሊሞች ምንም ተግባር ሳያከናውኑ፣ ፈረስ ሳይጋልቡ፣ ሰይፍ ሳይጨብጡ፣ ሱንናን ሳይዙ፣ ምግቦቻቸውንና መድሃኒቶቻቸውን ሳያመርቱ፣ በህይወታቸው ላይ በአላህ ህግ እስካልተፋረዱ እጆቻቸውን ዘርግተው ፍልስጤምን እንዲመልስላቸውና ይህን መከራ እንዲያነሳላቸው ቢጠይቁ ሊፀና አይችልም።

ከጌታችን ጋር ካልታረቅን፣ ህጉን ካልተገበርን፣ ከወንጀሎቻችን በንስሃ ካልተመልስን፣ ዱንያን ከቀልቦቻችን ካላወጣን፣ በልቦናችን ውስጥ ጀነት ካልገዘፈ...ከውርደት ወደ አሸናፊነት፣ ከደካማነት ወደ ኃያልነት፣ ከመናቅ ወደ ምቾት (መደላደል) ሁኔታችን ሊቀየር አይችልም።

እንዲህ ካደረግን የዚህ ሰዓት ህይወታችን በሙሉ እንቅስቃሴችንም ሆነ እርጋታችን ለፍልስጤም ጉዳይ ድጋፍ ይሆናል ማለት ነው።

- በጀመዓ የምንሰግደው ሰላታችን፣ ቁርአን መቅራታችን፣ ዚክራችን፣ ፆማችን...ሁሉም የሀይማኖታችንና የመታዘዛችን መገለጫዎች በሙሉ ለፍልስጤም ድጋፍ ይሆናሉ።
- ለወላጆቻችን በጎ መዋል፣ ዝምድና መቀጠላችን፣ ጎረቤታችንን መጠበቅ፣ መንገድን መንከባከብ፣ የተቸገረን ማገዝ... ሌሎችም የሙዕሚን ስነ ምግባሮች ሁሉም ለፍልስጤም ድጋፍ ይሆናሉ።
- እንዲሁም በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል፣ ሰዎችን ወደ ተሻለ ነገር መጣራት፣ ...እኒህም ለፍልስጤም ድጋፍ ይሆናሉ ማለት ነው።

ልክ እንደዚሁ ሙስሊሞች ወደ አላህ መልካም መመለስን ከተመለሱና ጠንካራ የሆነውን ዘለበት ከጨበጡ ሙሉ ህይወታችን ለፍልስጤም ድጋፍ ይሆናል ማለት ነው።

የፍልስጤም ጉዳይ ያለጥርጥር የሙስሊሞች ጉዳይ ነው። አንድ ቀን ወደ ኢስላምና ሙስሊሞች መመለስዋ አይቀርም። ዋናው ነገር ግን...ማን ነው ሚመልሳት? ወይም ደግሞ እንዲህ በል፡-

ማን ነው ወደ አላህ ተመልሶ...አላህ ደግሞ ፍልስጤምን የሚመልስለት?

<u>የመጨረሻ ንግግር</u>

ሙስሊሞች ላይ ስራ (ተግባር) ብቻ ነው ያለባቸው። ውጤት እነርሱ ላይ የለባቸውም። አላህ ባስቀደምነው ስራ እንጂ አይተሳሰበንም። "በዚህ ስራ ውጤቱ መጥቷል ወይስ አልመጣም?" ብሎ አይጠይቀንም።

የረሱል ﷺ ታሪክ በዚህ ምስክሮች የተሞላ ነው። የታሪክ ገፆችም እንዲሁ፡-

- ለኢስላም ምንም አይነት ድል ሳይመዘገብ በፊት መካ ላይ የተሰውትን ያሲርንና ሱመያን (ረዐ) ማን ነው ከምንዳ ሚነፍጋቸው?
- በኡሁድ ፊትና የተሰዋውን ሙስዓብና ሰባ ሸሂዶችን (ረዐ) ማን ነው ከምንዳ ሚነፍጋቸው? ድልን ባያዩም እንዳውም ነፍሶቻቸውን ያጡት ቁስል ሙስሊሞችን በወረረበት ሰዓት ቢሆንም ማን ነው እነሱን ከሰማዕታት ደረጃ የሚያወርዳቸው?

- ሙስሊሞች በሚያሳልፉት ከባድ መቅስፍትና አደገኛ ሁኔታ የተሰውትንና የሚጠበቅባቸውን ያበረከቱትን እነ ኹበይብ ኢብኑ ዐዲይና ሀራም ኢብኑ ሚልሃን (ረዐ) ማን ነው ከምንዳ ሚነፍጋቸው?
- እንደውም በል ...ማን ነው ሰልሃዲን አል አዩቢ የወጣበትን ትውልድ የሰሩ፣ የፍልስጤምን ነፃ መውጣት ሳይመለከቱ ጌታቸውን የተገናኙትን እነ ሚማዱዲን አዝዚንኪና ኑረዲን አዝ ዚንኪን ከምንዳ ሚነፍጋቸው?

ይህንን ጉዳይ ሙስሊሞች በተለይ የፍልስጤምንና የሐማስ መንግስት እያሳለፈው በሚገኘው ከባድ ወቅት በደንብ ሊረዱት ይገባል። ይህም አንዳንዶች "የሐማስ መንግስት ይህ ሁሉ ጫናና ከውስጥም ከውጭም በሚደረግበት ከበባ ተቋቁሞ መቀጠል አይችልም። ዛሬ ወይም ነገ ይወድቃል። ስለዚህ እና ልንቀሰቅሰው ምንሯሯጥለት ጉዳይ መቀየር

የማንችለውን በመጨረሻ መውደቁ ለማይቀር ነገር ነው።" ሊሉ ይችላሉ።

ከሙስሊሙ አዕምሮ ውስጥ መጥፋት የሌለበት ነገር "ስራ (ተግባር) እንጂ ውጤት አልተጠየቅንም" የሚለው አረዳድ ነው። የሐማስ መንግስት ወደቀ እንበል። ይኼ ከአላህ ጋር ያለህ ስራ ላይ ተፅዕኖ ያመጣልን? አላህ ሙዕሚኖችን የረሱል ﷺ የውሸት የሞት ዜና ሰምተው የተቀመጡትን እንዲህ ሲል ከንኖዋቸዋል "***ሙሐመድም ከበፊቱ መልዕክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ መልዕክተኛ እንጂ ሌላ አይደለም። ታዲያ ቢሞት ወይም ቢገደል ወደ ኋላችሁ ትገለበጣላችሁን ወደ ኋላው የሚገለበጥም ሰው አላህን ምንም አይጎዳም። አላህም አመስጋኞቹን በእርግጥ ይመነዳል።"***(አለ ሚምራን 144)

ሲዲቅ ረሱል ﷺ የሞቱ ጊዜ ይቺን አንቀፅ ጨብጦ ዘልዓለማዊውን እውነትን በተግባር አፀኑት። "ሙሐመድን የሚያመልክ ካለ ሙሐመድ ሞቷል።

አላህን የሚያመልክ ካለ አላህ ሕያው የማይሞት ነው...”

አንተ ለአላህ እንጂ ለሐማስ አይደለም ምትሰራው። የሐማስ መንግስት ቆመም ወደቀም (ለነርሱ አላህን ፅናት እንለምናለን) ስራችንን ለሚያይና ለሚቆጣጠር (ስራችን) አስከትሎት በሚመጣው ውጤት ሳይሆን በስራችን ላይ ምንዳ ለሚከፍለን አላህ ነው ምንሰራው።

ለኢስላምና ለሙስሊሞች ድልና ምቾት (መደላደል) (በፍልስጤምም ሆነ በሌሎች) የርሱ የራሱ (የአላህ) መብት ነው። በፈለገበት መንገድና በፈለገበት ሰዓት ያመጣቸዋል።

<u>በመጨረሻም...</u>

ይህንን ገጾች የጀመርኩበትን ደጋግሜ እላለሁ፡-

አቤት የንግግር መቅለል...አቤት የተግባር መክበድ... ሁሉም ሰው ንግግርን፤ በንግግሩም ስሜቱ መነካቱን መሰየት ይችላል። ተግባርን ግን ዕውነተኞች እንጂ አይችሉትም፡-

"የዐረብ ዘላኖች <<አምነናል>> አሉ። <<አላመናችሁም፤ ግን ሰልመናል በሉ። እምነቱም ገና በልቦቻችሁ ውስጥ ገና (ጠልቆ) አልገባም። አላህንና መልዕክተኛውንም ብትታዘዙ ከሥራዎቻችሁ ምንንም አያጎድልባችሁም። አላህ መሓሪና አዛኝ ነውና>> በላቸው።" (ሑጁራት 14)

አላህን ዕውነተኞችና ታጋዮች እንዲያደርገን፣ ፍልስጤምን ሙሉ ለሙሉ ነፃ እንዲያወጣልን፣ ሙስሊሞችን በምድር ውስጥ በምዕራብም በምስራቅም ያለውን እንዲረዳ፣ በሙጃሂዶች

መካከል ልቦቻቸውን እንዲያስተሳስርላቸው፣ የሙስሊሞችን ባንዲራ ከፍ እንዲያደርገው፣ ኢስላምና ሙስሊሞችን ከፍ እንዲያደርግ፣ ዕውነትን ዕውነት አድርጎ እንዲያሳየንና መከተሉን እንዲለግሰን፣ ውሸት ውሸት አድርጎ እንዲያሳየንና መራቁን እንዲለግሰን እንለምነዋለን!!!

እንዲሁም አላህን መንገዱን እንድንረዳ እንዲያደርገን፣ ሚጠቅመንን እንዲያስተምረን፣ ባስተማረን ነገር ላይ እንዲጠቅመን እንለምነዋለን። እርሱ ይህን አዋቂና ቻይ ነውና!!

<<ወደ ፊትም ለእናንተ የምላቸሁን ምክር (ቅጣትን በምታዩ ጊዜ) ታስታውሳላችሁ። ነገሬንም ሁሉ ወደ አላህ አስጠጋለሁ። አላህ ባሮቹን ተመልካች ነውና።>> **(ጋፊር 44)**

فداك أبي وأمي يا رسول الله



ስለዚህ ፍልስጤም የዑማው ኢማን መመዘኛ ናት።
ዑማው በፍልስጤም ጉዳይ ላይ በከፍተኛ ጉጉት
ከተንቀሳቀሰ ይህ የኢማን ጥንካሬ ምልክት ነው።
ዑማው በፍልስጤም ጉዳይ ከተዘናጋና ወደኋላ
ከቀረ የኢማን መድከም ምልክት ነው።
ድል ደግሞ ከደካማ ኢማን ጋር አይመጣም።

ከመፅሐፉ የተወሰደ

አንተ እና ፍልስጤም

2016 2024